


# ውይይት





ታህሳስ 2016
ቅፅ ፫ | ቁጥር ፬

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ
በየሩብ ዓመቱ በኲዊር ኢትዮጵያ
የምትታተም መጽሔት
Nisnis - A quarterly magazine
published by Queer Ethiopia
focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret



# ማውጫ




03



04 - 13



14 - 16



17



18 - 19



20 - 23



24 - 27



28 - 31



32 - 35



36 - 39



40 - 43

የኢትዮጵያ LGBTQ+ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ መርዛማ ባህሪያት ጋር ያጋጠሙዎት አለ እና የመከባበር ባህልንስ እንዴት መፍጠር እንችላለን?
44-00

# የአርታዒያን መልዕክት

በዚህ የኩዊር ሰዎች ጠል ማህበረሰብ ድንበር ላይ ቤታቸውን ለሰሩ ኩዊር ሰዎች  ማህበረሰባችን እስትናፋሳችን ነው። ማህበረሰቦቻችን ትክክለኛ ማንነታችን የምንሆንባቸው አስተማማኝ ቦታዎችን ይሰጡናል፣ መደጋገፍ እና መወደድ የምንችልበት የመረዳጃ ቦታዎችን ይሰጡናል፣ እና በዚህ ኩዊር ጠል ማህበረሰብ ውስጥ ሆነን ህይወታችንን በሰላም ለመምራት ልዩ ወሳኝ ግብዓቶችን እና መረጃዎችንም ይሰጡናል። የዚህ ውብ እና የማይበገር ማህበረሰብ አካል በመሆን የሚመጣው ብዙ ሳቅ፣ ፍቅር፣ ደስታ እና ሰላም አለ።

ነገር ግን፣ የእኛ የኩዊር ማህበረሰብ አስገራሚ ቢሆንም፣ ማህበረሰባችን ከተወሳሰቡ ነገሮች ጋር አብሮ እንደሚመጣም እንገነዘባለን። እና በሚያሳዝን ሁኔታ እነዚህ ውስብስቦች ልብ የሚሰብሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ አሥረኛው የንስንስ እትም ውስጥ ከሚያገኟቸው ጥቂቶቹ፡-

በሰውነት አቋም ማሸማቀቅ: “አንቺ ግን ለምንድነው ስፖርት የማትሰሪው? እኛም እንደዚህ አይነት ጊዜ እንድናሳልፍ መክሳት አለብሽ!”  በፍቅረኛዋ አንዷት ሌዝቢያን የተባለችው ነው።

የቅርብ አጋር (ፍቅረኛ) ጥቃት: “ከማንም ዓይነት ሰው ጋር እንድገናኝ ወይንም እንዳወራ አትፈልግም። በአላፊው በአግዳሚው ትጠረጥረኛለች እናም ሌላ ነገር አለሽ እያለች ታስቸግረኛለች። አንድ ጊዜማ ጭራሽኑ በቢላ ልታስፈራራች ሞክራለች” ትለናለች ሌላ ኩዊር ሴት።

ማንነትን አጋልጣለሁ በማለት ማስፈራራት: “ለቤተሰብሽ እናገራለሁ እና የመሳሰሉት ነገሮችም በጣም የተለመደ ነው። ... እኔ በቅርብ ጊዜ እራሱ እንደዚህ አይነት መልእክት ተልዕኮልኛል። ‘እንደዚህ አይነት ፎቶግራፍ ስላለኝ ችግር የለውም የማደርግሽን ነገር እኔ አውቃሉ’ ብለውኝ ያውቃሉ። ‘ስራ ቦታሽ እመጣለሁ፣ እናገርልሻለሁኝ፣ እበጠብጥሻለሁ’ የሚለው እንዳለ ነው። ወሬ ብቻም አይደለም በተደጋጋሚ የስራዬ ቦታ ትመጣ ነበር ...” ግሎሪያ ያለፉትን ግንኙነቶቿ በማስታወስ ትናገራለች።

ብሄርተኝነት: “ለምሳሌ ብላይንድ ዴት ላይ ለመውጣት እንኳን ካንቺ ጋር የምትስማማ አሪፍ ልጅ አለች ስትባይ ራሱ አማራ ከሆነች፣ ኦሮሞ ከሆነች፣ ከትግራይ ከሆነች ወይም የሆነ ዘር ጠርተሽ እንደዛ ካልሆነች አልፈልግም የመባባል ነገር አለ” ትላለች ህብስት።

የቦታ ክልከላ፡ “በኩዊር ስብሰባዎች ወይም ፓርቲዎች ላይም እንኳን የመጋበዝ ዕድል ብዙም የለንም። ሰዎች በቀላሉ እኛን መጋበዝን አያስታውሱም ምክንያቱም እኛን እንደ የኩዊር ማህበረሰብ አካል አድርገው አያስቡንም” በማለት ትናገራለች አንዷት ፓንሴክሿል ሴት።

ሀሜት፡ “ሀሜት እና ወሬ በጣም ይናፈሳል፤ እገሌ እንደዚ ብላለች በዚህ መልስ ሰጠች የሚባሉ ብዙ የወሬ ማቀባበሎች ያጋጥመኛል። ጉዳይሽ በሙሉ በቀላሉ ሁሉ ቦታ ይደርሳል” ትላለች አንድ በተደጋጋሚ ይህ ሁኔታ ያጋጠማት።

በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉት የመርዛማ ነገሮች ዝርዝር ማለቂያ ያለው አይመስልም። ማህበረሰባችን ራስን ለመግለጽ እና ራስን ለመቀበል ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታዎችን ቢያቀርብልንም፤ ያልተመረመሩ፣ አድሎአዊ ድርጊቶችን እና መፍትሄ ሊሰጣቸው የሚገቡ መርዛማ ነገሮችንም ይይዛል።

ይህ የንስንስ እትም እራሳችንን እንደ ማህበረሰብ አጥብቀን እንድንጠይቅ ያስችለናል። መመርመር ያለብን ቦታዎች የትኞቹ ናቸው? ይህንን ማህበረሰብ ለሁላችንም ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? በማህበረሰባችን ውስጥ መርዛማነትን እንዴት በብልሃት እንፈሻለን እና እንዴትስ እንጋፈጣለን?

ለሁሉም መልሶች የሉንም። እኛ ግን እንደ ማህበረሰብ ውይይቱን ለመጀመር ወሳኝ እርምጃ ለመውሰድ ወስነናል። ውይይት በኛ እና ለእኛ።

እንደሁሌው በዚህ የንስንስ እትም ላይ የበኩላቸውን ላደረጉ ሁሉ ምስጋናችን ከልብ ነው። በዚህ ውይይት ላይ አሁንም በቀጣይነትም ስለምትሳተፉ ሁላችሁንም እናመሰግናለን እንላለን።

# ውይይት፡ በኲዊር ማህበረሰባችን ውስጥ መርዛማነትን እና አድሏዊነትን መመርመር





ለብዙዎቻችን LGBTQ+ ሰዎች፣ የኲዊር ማህበረሰብ ብዙውን ጊዜ የመረጥነው ቤተሰባችን ነው። ምቾት የሚሰማን ቦታ ነው። ትክክለኛ ማንነታችን የምንሆንበት ነው። ኲዊር በመሆናችን እንደማንገለል እርግጠኛ የምንሆንበት ቦታ ነው። ይህ ለሁሉም የኲዊር ሰዎች አስፈላጊ ቢሆንም በተለይ ስር የሰደደ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት እንደባህል የተያዘበት ኢትዮጵያ ላይ በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ የኲዊር ማህበረሰቦች ለህልውናችን ያለውን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ጉድለቶቻችንን መመርመር መቻል ወሳኝ ነው።

አምስት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴቶች በማህበረሰባችን ውስጥ መስተካከል ስላለባቸው ያልተመረመሩ አድልዎ እና መርዛማ ልምዶችን ይወያያሉ። ውይይቱ ለቦታ እና ግልጽነት ተስተካክሏል።



ንስንስ፦ የኲዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያጋጠማችሁ መርዛማ የሆኑ ባህሪዎች ወይንም ነገሮች አሉ? ካሉስ ምንድን ናቸው?

ዮሐና፦ እኔ በግሌ የገጠመኝ ነገር   ባይሆንም መድልዎ እና ሀሜት እንደማንኛውም ማህበረሰብ እኛም ጋር አለ።

ህብስት፦ እኔንም ያጋጠመኝ አንዱ መርዛማ ነገር ሃሜት እና ወሬ ነው። የፍቅር ግንኙነት ውስጥ እየነበርኩኝ ወሬ ያስቸግረኝ ነበር። ማህበራዊ ሚዲያ ውስጥ ደግሞ የመጀመሪያ ጊዜ ስትገቢ በጣም ትኩረት ይሰጥሻል። አብዛኛዎቹ ማህበራዊ ሚዲያ ውስጥ ያሉ የኲዊር ማህበረሰብ ፍሬንድ ሪኩዌስት ይልኩልሻል። ሊያናግሩሽ ወይንም ጓደኛ ሊያደርጉሽ ይፈልጋሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ የምትሰሚው ነገር አለ፤ ራስሽም ልትታሚ ትችያለሽ። ሌላው መርዛማ ነገር ደግሞ ሴታ ሴት ወይንም ወንዳወንድ መባልሽ ነው። እርስ በርሳችን ስንሰባሰብ ወንዳወንድ ወይንም ቡች ማን ናት ይባላል። ሴታሴት ሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለ። እንደፈለግሽ ስትሆኚ ወደ አንዱ እንድትሄጂ ትንሽ ጫና ይደረግብሻል።

ኤክስ፦ እኔ አሁን የነበረኝ የመጨረሻ ግንኙነቴ ላይ ብዙ የግል መረጃዬ ስለነበራት ለቤተሰብሽ አሳልፌ እሰጣለሁ በማለት አስጨንቃኝ ነበር። እኔም ትሰጣለች ብዬ ተዘጋጅቼ እየጠበኩኝ ራሴን ለማጋፈጥ ዝግጁ ሆኜ ነበር። ያመንሽው ሰው እንደዚህ ሊያጋልጥሽ ሲሞክር የአይምሮ ጭንቀት ያመጣል። ይሄ ማጋለጥ እና ማስፈራራት አንድ የመርዛማ ምሳሌ ነው።

ማራኪ፦ በሃሜት ዙሪያ ቡች የሆኑ ሴቶች ላይ የሚያጋጥም ነገር አለ። ብዙ ሰው እኛ ማህበረሰብ ውስጥ ቡች ሴቶች የበላይ መሆን እንደሚፈልጉ እና ሃይለኛ እንደሆኑ ያወራል። እኔ የማስበው ግን አንድ ሴት ሴታሴትም ሆነች ቡች የባህሪይ ጉዳይ ነው እንጂ ሃይለኝነት ወይንም መርዛማ መሆን ለቡቾች ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ነው ብዬ አላስብም። እናም ጉልበተኛ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰቡ አላስፈላጊ የሆኑ ስሞች ለጥፈውብሽ ይጠብቁሻል። ለረጅም ጊዜ አብሬ የቆየኋት የቀድሞ የፍቅር ጓደኛዬም ጋርም መርዛማ የሆነ ነገር ነበር። ብዙ ስም የማጥፋት ነገር ነበር፤ ሃይለኛ ናት ጉልበተኛ ናት የሚል ሃሜት ተመልሶ አንቺ ጋ ይደርሳል ሰውም አንቺን ምንም ሳያውቅሽ እንደዛ አይነት ወሬ ሲቀባበል ይውላል እና ይሄ አንድ ወቅት ላይ በጣም የጎዳኝ ነገር ነበር። ቡች በሚለው ስብእና ውስጥ ስላለሽ እና በሆኑ ሰዎች ላይ ስለ ቡች የሆነ አመለካከት ስላለ እውነት ይሁንም አይሆንም እንደሚባለው ናት ለማለት ምንም ማሰብ አያስፈልጋቸውም።

ግሎሪያ፦ እኔም ብዙ መርዛም የሆኑ ነገሮች ገጥመውኛል። አሁን በጣም ያስቸገረኝ ነገር አድብቶ መከታተል (stalking) ነው። በተለያየ ስልክ ቁጥር በተለያየ አካውንት ሰውን ለማግኘት መሞከር የተለመደ ነው። ለቤተሰብሽ እናገራለሁ እና የመሳሰሉት ነገሮችም በጣም የተለመደ ነው። እኔ በቅርብ ጊዜ እራሱ እንደዚህ አይነት መልእክት ተልዕኮልኛል። “እንደዚህ አይነት ፎቶግራፍ ስላለኝ ችግር የለውም የማደርግሽን ነገር እኔ አውቃሉ” ብለውኝ ያውቃሉ። “ስራ ቦታሽ እመጣለሁ፣ እናገርልሻለሁኝ፣ እበጠብጥሻለሁ” የሚለው እንዳለ ነው። ወሬ ብቻም አይደለም በተደጋጋሚ የስራዬ ቦታ ትመጣ ነበር እና ፈርቼ፣ ሼም ይዞኝ እና ስራ ቦታ ድራማ እንዳይፈጠር ምንም አማራጭ የለኝም እሺ ብዬ ተቀብዬ አቅፌያት እሄድ ነበር።  ሌላ ደግሞ መቆጣጠር (controlling) ነው። ክሮፕ ቶፕ መልበስ አትችይም፣ ቀሚስ መልበስ አትችይም፣ በግዴታ ሁሉ ጊዜ ልብስሽን እና እና አለባበስሽ ላይ እሷ ከምትፈልገው ውጭ እንድትሆኝ አትፈልግም። ያው ሌላ በገንዘብና በብርም “እኔ ወንዳወንድ ስለሆንኩኝ ብሩ እኔ ጋ ይሁን ወንድ ሂሳብ ሲከፍል ነው የሚያምረው” የሚባል ነገር አለ። የሚገርምሽ በዛን ጊዜ ይህንን ነገር ተቀብለሽ ትኖሪያለሽ።

ህብስት፦ የምትወጂው ሰው ላይ ሲሆን ዝም ብለሽ የምትቀበይው ነገር አለ። ቡቾች ላይ ሲሆን ግን የሚጠብቅ ነገር አለ። ቦልድ ሆና የምትጠጋሽ ወይንም የፍቅር ጥያቄ ቀድማ የምታነሳው ቡች የሆነች ናት ተብሎ ይጠበቃል። ወይንም ብር ያላት መሆን አለበት። ፌም የሆነችዋ እንደዛው ማድረግ ብትፈልግ ቡችዋ ላይመቻት ይችላል። አንዳንድ ፌም ሴቶች ደግሞ የሚፈልጉት ሌላ ፌም ሴት ነው። ሰዎች የተሰበሰቡበት ቦታ ስትሄጂም የሚጠበቅ እና እንዲታይልሽ የሚፈልግ ነገር አለ።

ማራኪ፦ በራስ መተማመን አለሽ ብለው የሚያስቡት አንቺን ነው። አንቺ አርጊው፣ አንቺ ተወጪው ይሉሽ ፤ አንቺ ደሞ ሃላፊነት ተሰምቶች እነሱን ያገዝሽ መስሎች ታደርጊዋለሽ። ከዛ ግን ለመቆጣጠር ትፈልጋለች ተብሎ ስምሽ ይጠፋል።

ንስንስ፦ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለው ግንኙነታችን ምንድነው የሚመስለው?

ግሎሪያ፦ እኔ የኛ ማህበረሰብ ላይ ከሚደብርኝ ነገር ውስጥ አንዱ ሰው እርስ በርሱ አለመነጋገሩ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ማራኪ ጋር ቢፅፍ እና እሷ ቶሎ ከመለሰች “ሙድ” የላትም ብሎ ነው ብዙ ሰው የሚያስበው። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተጫዋች መሆን “ሙድ” እንደሌለው ነው የሚታየው። መነጋገር የማንችል ከሆነ አንዷ መጥታ የሆነ ነገር ትለኛለች ውሸትም ሊሆን ይችላል እኔ ሄጄ እንደዚህ እንደዚህ ተብያለሁ እውነት ነው ወይ ብዬ መጠየቅ አልችልም ምክንያቱም ማንም መልስ አይሰጠኝም። በመሃላችን መነጋገር የለም።

ህብስት፦ ሌላ ኲዊር ማህበረስቡ ውስጥ ካሉት ሰዎች ጋር ተግባቢ አይደሉም። ደስታ የሚሰጣቸው አዲስ ሰው ነው። አዳዲስ ሰው ካልሆነ



የሚያወቁትን ሰው ለማውራት ብዙም ዝግጁ አይደሉም። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ በጓደኝነት (Friendship) ነው ማውራት የምፈልገው ካልሽ ማንም ሰው መልስ አይሰጥሽም።

ማራኪ፡- "ጓደኝነት ብቻ ነው የምፈልገው" ካልሽ ማንም መልስ አይሰጥሽም። መልስ የሚሰጥሽ ሌላ ግንኙነት የምትፈልጊ ከሆነ ነው።

ዮሐና፡- ኦንላይን ላይ ወንዶች ሆነው ኲዊር ሴት እንደሆኑ አድርገው የሚቀርቡ አሉ። ያኔ ገና ስጀምር እንደዚህ ተሳስቼ አውቃለሁ። በስልክ ሁሉ ስናወራ ሴት ነው የምታወራኝ የመሰለኝ ከዛ ግን በአካል ሄጄ ተቀጣጥርን ስሄድ ወንድ ነው። ያኔ አዲስም ነበርኩኝ አዲስ አበባንም በደንብ አላውቃትም ነበር። በጣም ደንግጬ ነበር ልቤም በጣም ነበር የተሰበረው። ዝም ብዬ ተመለስኩኝ፤ ልጁ ምንም አላደረገኝም ግን ቢፈልግ ኖሮ ፎቶዬም ድምፄም ነበረው። ሌላ ደግሞ መጀመሪያ ወደ ማህበራዊ ሚዲያ እንደመጣሁ አንድ ሴት ነበረች ፎቶሽን እለቅብሻለሁ ያለችኝ። በአብዛኛው ግን ጉዳቱ የደረሰብኝ ከኲዊር ማህበረሰብ ሳይሆን የማህበረሰብ ሚዲያ አጠቃቀሙን አለማወቄ ነበር።

ግሎሪያ፡- እኔ የማስፈራራት ነገር ገጥሞኛል። እንደውም የድሮ የፍቅር ጓደኛዬ ከማስፈራራትም አልፎ ያለፍቃዴ ለኲዊር ሰዎች ስልክ ቁጥሬን ሰጥታ አስታርቁኝ ብላቸዋለች። እናም ያለፍቃዴ ብዙ ሰዎች ስልክ ቁጥሬ አላቸው። ከፌክ አካውንት አልፎም የእውነተኛ አካውንት፣ ሙሉ የመኖሪያ ቤት እና የስራ ቦታ አድራሻ የተሰጠበትም አጋጣሚ ነበር።

ንስንስ፡- ሌላስ እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በዘር፣ በሃይማኖት እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ዙርያ መርዛማ ልምዶች አሉ?

ግሎሪያ፡- አፍ አውጥተው "የኔ ዘር ካንቺ ይበልጣል" አይሉሽም ግን "እኔ የመጣሁበት አካባቢ ከመጣሽበት አካባቢ ይሻላል" ይሉሻል። በግልፅ "እኔ እየመጣሁበት ከተማ ከመጣሽበት ከተማ እጥፍ ይበልጣል" ተብያለሁ። "ትግራይ ላይ ያለው ጦርነት ይደብራል መቆም አለበት" ስል ዘረኛ ነሽ ተብያለሁ። የራስሽን ቋንቋ የሚያወራ ሰው ስታገኚ ደስ ይላል ምክንያቱም ከዚያ ሰው ጋር የሚያስተሳስርሽ ነገር ስላለ። ከዛ ሞቅ እና ደስ ብሎኝ ሳወራ "ቋንቋ ቀይራችሁ የምታወሩት ዘረኛ ስለሆናችው ነው" ተብለናል። እሷ ግን የራሷ ቋንቋ የሚያወራ ሰው ስታገኝ ደስ ብሏት ከሁለቱ ውጪ ሌላ ሰው እንደሌለ አድርጋ ሞቅ አርጋ ታወራለች። እና የሆነ ምክንያታዊ ያልሆነ ነገር አለ።

ህብስት፡- ዴት ስትደራረጊ በዘር የመመራረጥ ነገር አለ። የራሴ ዘር ካልሆነ ዴት አላደርግም የሚል ብዙ ሰው አለ። ለምሳሌ ብላይንድ ዴት ላይ ለመውጣት እንኳን ካንቺ ጋር የምትስማማ አሪፍ ልጅ አለች ስትባይ ራሱ አማራ ከሆነች፣ ኦሮሞ ከሆነች፣ ከትግራይ ከሆነች ወይም የሆነ ዘር ጠርተሽ እንደዛ ካልሆነች አልፈልግም የመባባል ነገር አለ። እኔ እሷ የፈለገቸው ዘር ስላልሆንኩኝ አልፈልግሽም ተብዬ አውቃለሁ።

ንስንስ፡- ኲዊር ማህበረሰብ አንቺን አያጠቃልልም ስለዚህ እዚህ

"'ጓደኝነት ብቻ ነው የምፈልገው' ካልሽ ማንም መልስ አይሰጥሽም። መልስ የሚሰጥሽ ሌላ ግንኙነት የምትፈልጊ ከሆነ ነው።"
ማራኪ

## “እኔ የኛ ማህበረሰብ ላይ ከሚደብርኝ ነገር ውስጥ አንዱ ሰው እርስ በርሱ አለመነጋገሩ ነው።” ግሎሪያ

አትጋበዥም የሚል ሁኔታ ገጥሟቸኋል?

ህብስት፡- ብዙ ባይሴክሽዋል ጓደኞች አሉኝ እና ጓደኞቼ የኲዊር ማበረሰብ ስብስብ ላይ ብዙም አይጋበዙም። ልባቸው የት እንደሆነ ግልፅ አይደለም የሚለው አንድ ምክንያት ነው። ማንነታችንን ሊያጋልጡም ይችላሉ ብለው ይታሰባሉ። ይህም ባይሴክሽዋል ወይንም ባይኪውሪየስ የሆኑ ሰዎች እንደ ሌዝቢያን ሰዎች የተደበቁ አይደሉም፤ ሰው ቢያውቅም ምንም ላይመስላቸው ይችላል የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ስላለ ነው። ስለዚህ የኲዊር ማህበረሰብ ስብስብ ሲኖር እነሱን ያለመጥራት ሁኔታ አለ።

ዮሐና፡- ያው ያለው ነገር ባይሴክሽዋል ሲሆኑ የበለጠ ሴፍ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ይመስለኛል። የሆነ ነገር ከመጣ እነሱ አንድ ወንድ ጠብሰው በዛው ማምለጥ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። አንዷ ባይኪውሪየስ ጓደኛዬ “ሲያስጠሉ! ወንዶቹ ግን ለምንድነው ጌይ የሚሆኑት?” ብላኝ ታውቃለች። ስለ ወንዶቹ ዛሬ ይህንን ካለች ደግሞ ስለኛ ሴቶቹ ምን ትላለች ብዬ አስቤያለሁ። ይህ ግን ባይኪውሪየስ በመሆኗ ሳይሆን ለራሷ ካላት ጥላቻ የመጣ ነው። እንደዚህ አይነት ነገር በአብዛኛው ራሱን ከተቀበለ ሰው አይመጣም እና እነሱን ከመጥላት የመጣ ሳይሆን ከፍራቻ የመነጨ ነው።

ግሎሪያ፡- እኛ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ግሩፖች አሉን። የእነንትና ግሩፕ የእነንትና ግሩፕ የሚባል ነገር አለ። የኲዊር ማህበረሰብ ስብስብ ወይም ፓርቲ ሲኖር ሰው የሚጠራራው በግሩፑ ነው። ማራኪ የራሷን ቡድን ትጠራለች፣ ዮሐና የራሷን ግሩፕ ትጠራለች። እንደው አንቺ ዝም ብለሽ ብቻሽን ብትሄጂ ብቻሽን ነው የምትሆኚው ምክንያቱም የሚያናግርሽ ሰው እንኳን አታገኚም። አንዱ ግሩፕ ከሌላ ግሩፕ አይቀላቀልም። የተወሰኑ ሰዎችም ሊያገሉሽ ወይም ጓደኛ ለማሳጣት ሲሞክሩ ሁላ “እኔን ወይም ቤስት ፍሬንድሽን ምርጪ” እና የመሳሰሉትን ነገር ይሉሻል።

ዮሐና፡- ስለ መርዛማነት ስናወራ አንድ ጓደኛዬ አንድ ጊዜ ከአዲስ ቡድን ጋር ተቀላቀለች ከዛ መሀል ዴት ልታደርጋት የፈለገች ሴት ብትኖርም እሷ ግን አልፈለገችም። እናም ስላልፈለገች የተወሰነ ያህል ከቡድኑ አግለዋት ነበር።

ማራኪ፡- ማህበረሰብ ማለት የዴት ማድረጊያ ድህረ ገፅ አይደለም። አንዳንዴ እኮም ሰው ለፍቅር ብቻ ነው የሚፈላለገው ማለት አይደለም። ምንም ነገር ሳይኖረን ተሰባስበን ጥሩ ጊዜ ልናሳልፍ እንችላለን። መሰባሰቦቹ ሁሉ በአብዛኛው ለዴቲንግ ብቻ ነው የሚመስለው። አንዴ የሆነ ቦታ ሄደን አይተነው ዴት ለማድረግ የሚመች ነገር ካልሆነ ለሌላ ነገር መሄድ እንኳን አንፈልግም። ይሄ አስተሳሰብ በፍጹም ትክክል አይደለም ይህንን ለመቀየር የግድ መሰራት ያስፈልጋል።

ህብስት፡- አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ግሩፕ ለምሳሌ ሲጠጣ እይታ ይስባል ስለዚህ እሱ ግሩፕ ያለበት ቦታ አንሄድም የሚል ነገር አለ።

ሌላኛው ግሩፕ ደግሞ ስርአት አድርገው ሳይንቀለቀሉ ስለሚዝናኑ እነሱ ጋር ትሄጃለሽ። ስለዚህ እንደ ስብስቡ ይለያያል። እኔም መጀመሪያ ማህበረሰብ ውስጥ ስገባ ለምንድነው የማይቀላቀሉት እል ነበር።

ግሎሪያ፡- በዛ ላይ የሆነ ነገር ሲወራ አንድ ግሩፕ ውስጥ ይወራል። እና አንቺም አንድ ቦታ ስትሄጂ ይሄን ያወራው ግሩፕ ካለ ገና ከአነጋገራቸው ለራስሽ ለምን መጣሁ ብለሽ እስኪቆጭሽ ድረስ ያደርሱሻል።

ንስንስ፡- ለምንድን ነው እነዚህ ግሩፖች የማይቀላቀሉት?

ግሎሪያ፡- ያው በአብዛኛው የኛ ግሩፕ ይሻላል የሚል እምነት ስላላቸው ነው። አሪፎቹ እኛ ነን ብለው ስለሚያስቡ ይመስለኛል።

ህብስት፡- አንዳንዱ ግሩፕ ደግሞ አሪፍ ስለሆንን ሰላም ነን ብሎ ያስባል። አንዳንዶቹ ደግሞ እኛ ድራማ የለንም ብሎ ያስባሉ።

ማራኪ፡- እውነትም በእርግጠኝነት እንደዚህ አይነት ግሩፕም እኮ አለ። አሪፍ ግሩፕ አለ ግን ጠጥቶ የሚበላሽም ግሩፕ አለ። እንደዚህ ማለት ቢደብረም እንደዚ አይነት ግሩፕ አለ። ስለዚህ ከእነርሱ መሸሸ ለኔ ደህንነት ነው ሌላ ምንም ምክንያት የለውም። ግን ምናልባት እነዛ ሰዎችን ወደ አንቺ ደግሞ ማምጣት ይቻላል። በግልጽ መጥፎ ሰዎች አለን። አሁን ስለ መርዛማነት ስናወራው እንደቆየነው ማለት ነው። እኔ ራሴ ለምሳሌ እነዚህ እነዚህ ሰዎች አሉ ከተባልኩኝ የማልሄድበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም እዛ ቦታ ሊፈጠር ይችላል ብዬ የማስበው ድራማ መከላከል ስለማልችል እና ለእኔ ምቾት የሚሰጠኝ ቦታ አይደለም ብዬ ስለማስብ መሄድ አልፈልግም። እና ይህ ለደህንነት ስለሆነ ለእኔ ምንም ክፋት የለውም።

ንስንስ፡- ጥሩ ብለን የምናስበው እና የምንፈልገው ኩዊር ማህበረሰብ ምን ይመስላል?

ኤክስ፡- አንደኛ ነገር እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ ተቀላቅዬ አላውቅም። ይሄም ብዙ ጊዜ ሴፍ አይደለም ብዬ ስለማምን ራሴን አግልዬ የምኖር ሰው ነኝ። ግን ትንሽ መነጋገር እና መግባባት ላይ ቢሰራበት የበለጠ ያቀርበኛል ብዬ አስባለሁ። ከማራኪ ጋር ሳወራ በጣም ተረዳኛለች እና አሁን እንደ ማራኪ አይነት ሶስት ወይንም አራት ሰዎች ቢፈጠሩ እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ እንደኔ ተደብቆ የሚኖር ሰው ያለ ስጋት ይወጣል። ሁኔታው ጥሩ ካልሆነ እኔም ራሴን የበለጠ እያሸሸሁኝ እመጣለው። ስለዚህ እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በግልጽ ውይይት ማድረግ የሚችሉ ሰዎች ቢኖሩ የተሻለ ነው ብዬ ነው የማስበው።

ዮሐና፡- ለምሳሌ ፌስ ቡክ ላይ ለጓደኝነት ብለሽ ከሰው ጋር ስትፃፃፊ የሚያቀራርብ ነገር ቢኖር ደስ ይለኛል ምክንያቱም አብዛኛው ሰው ፌስ ቡክ ላይ አክቲቭ ነው። ቢያንስ ፌክ አካውንት አለው። ለምሳሌ እኛ ቴሌግራም ላይ አንድ ግሩፕ ነበረን እና በጣም አሪፍ ነበር። እርስ በእርሳችን አንዳንድ ችግር ሊኖርብን ይችላል ግን ስንሰበሰብ ስለኩዊር

"ያመንሽው ሰው እንደዚህ ሊያጋልጥሽ ሲሞክር የአይምሮ ጭንቀት ያመጣል። ይሄ ማጋለጥ እና ማስፈራራት አንድ የመርዛማ ምሳሌ ነው።"
ኤክስ



ማህበረሰቡ ጥሩ ውይይቶች ነበሩ። የግድ ስለኩዊር ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ውጪ የሆነ ጓደኝነትም መመስረት እንደሚቻል አይቻለሁ፡፡ እሱ ግሩፕ ፈርሰዋል፤ ተመሳሳይ ግሩፖች ቢፈጠሩ ግን ደስ ይለኛል። በፊት ፓርቲዎች እና ስብሰቦች ነበሩ አሁን ብዙም የሉም። በተለይም ያኔ ከተፈጠረው ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል እንቅስቁሴ በኋላ ብዙም የሉም፤ እነሱ የበለጠ ቢኖሩ ሰውም የበለጠ ይቀራረባል ብዬ አስባለሁኝ። እንደዚህ ከኩዋር ማህበረሰብ ጋር ሳልሰበሰብ ስቀር የጠፋሁ ይመስለኛል። ለተቃራኒ ፆታ አፍቃሪ ጓደኞቼ መናገር እራሴን ሁሉ ማውጣት ያምረኛል። የታፈንኩኝ ያህል ሆኖ ይሰማኛል።

ንስንስ፡- ከነዚህ መርዛማ ልምዶች ሁሉ የፀዳ ማህበረሰብ እንዴት መመስረት እንችላለን?

ግሎሪያ፡- መጀመሪያ ሁላችንም እራሳችንን መገንባት ያስፈልገናል። አስተሳሰባችንን ለመቀየር መስራት አለብን።. እነዚህ ነገሮች ሊቀየሩ የሚችሉት ጤናማ የሆኑ ውይይቶች ሲፈጠሩ ነው። ሌላው በግልፅ መነጋገር ያስፈልጋል። ብዙ መርዛማ ነገርም የሚፈጠረው በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ነው። ስለዚህ ሰዉ ሲለያይ ወይንም አዲስ ፍቅር ግንኙነት ውስጥ ሲገባ ሁሉንም ነገር በግልፅ መነጋገር ያስፈልጋል።

ህብስት፡- ልክ ለራሳችን አሳቢ እንደምንሆነው ለሌላ ሰውም ጥሩ አሳቢ ብንሆን ጥሩ ነው። ለራሳችን ይቅርታ አድራጊ እና ተረጂ እንደምንሆነዉ ለሌላም ሰው እንደዛ ብንሆን ማህበረሰቡን ልንቀይር እንችላለን። በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል እንቅስቃሴው ወቅት እንደተባበርነው እና አንድ እንደሆንነው ብንሆን ጥሩ ማህበረሰብ መፍጠር እንችላለን።

ማራኪ፡- መርዛማ የሚባሉ ነገሮችን የሚያራምዱ ሰዎችን በቅርብ ብናወያይ እና ብንሰባስብ ከነዚህ ነገሮች እንዲቆጠቡ ማስተማር ይቻላል። ሁላችንም ስንሰበር መርዛማ ልንሆን የምንችል ሰዎች ነን። የተደበቀ ባህሪ ሊኖረን ይችላል እና እንደዚህ ነገሮች ሲፈጠሩ እነዛን ሰዎች ማግለል ሳይሆን፤ ጤናኛ የሆነ ማህበረሰብ ሲኖረን እነዚህንም ሰዎች እያሰባሰብን የተሻለ ማድረግ እንችላለን። መሰባሰቡም የሚጠቅመው መርዛማ የሆኑ አስተሳሰቦችን የሚያንፀባርቁ ሰዎች ጤናማ ከሚባለው የህብረተሰቡ አካል ጋር ሲሰበሰቡ ወደ ተሻለ ጤናማ ነገር ሊመጡ ይችላሉ። እኔ ችግር የለብኝም ማለቴ ሳይሆን ሁላችንም ስንገናኝ ግን ስብሰባዎቻችን ላይ በተሻለ መንገድ መማማር እንችላለን። መርዛማ የሆኑ አስተሳሰቦች እና የፍቅር ግንኙነቶችን ያለው ጤናማ የሆኑ የጓደኝነት ግንኙነቶችን ያያል ከዛ የተወሰነ ነገር እየተማረ ይመጣል። ብዙ አይነት ባህሪ አለን። የምንሰበርበት መንገድ የተለያየ ነው የመጣንበት የአይምሮ ጤናም የተለያየ ነው። ማንም መገለል የለበትም። ባህሪ ደግሞ ከጊዜ ወዲህ ይሻሻላል ስለዚህ እነሱ ላይ በደንብ እንስራ።

ኤክስ፡- ትምህርትም ማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ነው። የትምህርት ማነስ አንዳንድ ጊዜ ተጽዕኖ አለው ብዬ ነው የማምነው። ብዙ ሀሜቶች እና ወሬዎች የሚፈጠሩት አብዛኛው ሰው በግምት ስለሚሄድ ነው። በመረጃም ሆነ በማገናዘብ ትንሽ ወደኋላ የቀረን ነን። በኢኮኖሚ ያደጉ አገሮች ጋር ስትሄጂ እነሱ ስለሚያነቡ ስለሚያውቁ ሀሳባቸውን ስለሚያጋሩ ለዛ ማህበረሰብ ጠንካራ የሆኑ የጀርባ አጥንት ናቸው። የሆነ ሰው ችግረኝ ቢል ያግዛሉ እኛ ማህበረሰብ ጋር ስትመጪ ግን ይሄ ነገር ላይኖር ይችላል። ስለዚህ በተገናኘን ቁጥር መረጃዎች ብንለዋወጥ ብንማማር የተሻለ ለውጥ ማሳየት እንችላለን ብዬ አምናለሁ።

ግሎሪያ፡- ወሬ ማቀባበልም እናቁም።


ዮሐና፡- ማህበረሰብ ላይ በእድሜም በልምድም የቀዩ እና ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች የበለጠ ቢሳተፉ ለኛም የበለጠ ሴፍ የሆነ ሁኔታ ይፈጥርልናል።


“ሁላችንም ስንሰበር
መርዛማ ልንሆን
የምንችል ሰዎች ነን።
የተደበቀ ባህሪ ሊኖረን
ይችላል እና እንደዚህ
ነገሮች ሲፈጠሩ እነዛን
ሰዎች ማግለል ሳይሆን፤
ጤነኛ የሆነ ማህበረሰብ
ሲኖረን እነዚህንም ሰዎች
እያሰባሰብን የተሻለ
ማድረግ እንችላለን።”
ማራኪ



# የውይይት እና ራስን የመፈተሽ ጥሪ

ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ኩዊር ግለሰቦች በኩዊር፣ በተለይም በLBQ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት መርዛማ ልምዶችን ዋነኛ የሚሏቸውን ለይተው ለመዘርዘር ሞክረዋል። እነሱም ትራንስ ጠልነት፣ የባይ/ፓን ማንነት አለመታየት፣ የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀም፣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት፣ ውስጣዊ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት፣ ያለፍቃድ የሰውን ማንነት ማጋለጥ እና በኩዊር ማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ በፍቅር ጓደኝነት ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት መስጠት ናቸው።





የኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ሌዝቢያን የሚለውን ቃል “(በሙሉ ወይም በአብዛኛው) የወሲብ ወይም የፍቅር ስሜት ለሌሎች ሴቶች ያላት ሴት” ብሎ ይተረጉመዋል። ይህ መሰረታዊ ትርጉም ከተሰጠን በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለቡች ሴቶች ያላትን ፍላጎት ትርጉም መስጠት አለመቻላቸው ለሰላም እንግዳ ነገር ሆኖ አግኝታዋለች።

ሰላም ለተባለች ቡች ሴት ይህ ቡች ለቡች የፍቅር ግንኙነት ጠልነት በኢትዮጵያ ያለው ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት መርዛማ ልምዶች እንደ አንድ መገለጫ ታየዋለች።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠል አገሮች ውስጥ የLGBTQ+ ማህበረሰብ ኩዊር ሰዎች ተቀባይነት፣ ግንዛቤ እና መመሪያ የሚያገኙባቸውን ቦታዎች ይፈጥራሉ። እነዚህ ማህበረሰቦችም ጥላቻን የመቋቋም አቅምን ያጎለብታሉ፣ ግለሰቦችን ያበረታታሉ እናም ኩዊር ለሆኑ ግለሰቦች እራሳቸውን የመሆን እድሎችን ይሰጣሉ።

በአዲስ አበባ ውስጥ የምትኖረው ሌዝቢያን ማራኪ ማህበረሰቡ ጠቃሚ ቢሆንም በLGBTQ+ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉትን መርዛማ ልምዶችን በግልፅ መመርመር የበለጠ ጠንካራ እና ጤናማ የኩዊር ማህበረሰብ ለመገንባት አስፈላጊ መሆኑን ገልጻለች።

ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ኩዊር ግለሰቦች በኩዊር፣ በተለይም በLBQ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት መርዛማ ልምዶችን ዋነኛ የሚሏቸውን ለይተው ለመዘርዘር ሞክረዋል። እነሱም ትራንስ ጠልነት፣ የባይ/ፓን ማንነት አለመታየት፣ የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀም፣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት፣ ውስጣዊ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት፣ ያለፍቃድ የሰውን ማንነት ማጋለጥ እና በኩዊር ማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ በፍቅር ጓደኝነት ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት መስጠት ናቸው።

ሰላም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን መርዛማ ልምዶች በሁለት ትከፍለዋለች። አንደኛው በግለሰብ ደረጃ ያለ መርዛማነት ሲሆን ሁለተኛው እንደ ማህበረሰብ ያሉት ናቸው። በግላዊ ደረጃ ቢያንስ ሶስት የመርዛማ ልምዶችን ለይታለች። እነሱም ያለፈቃድ የግል ታሪኮችን መጋራት ፣ ሰውን አስፈራርቶ የሚፈልጉትን ማግኘት ልምድ እና በማኅበራዊ መደብ፣ በቋንጅና፣ በትምህርት ደረጃ እና በዘር

ምክንያት የላቀ የመሆን ስሜት መኖር ናቸው።

በማህበረሰቡ ደረጃ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ልምድ ያሳስባታል። “ዕፅ አላግባብ መጠቀም ከ’ኩዊር ማህበረሰብ’ ጋር ተለዋዋጭ እየሆነ ቢመጣም እና ከሰፊው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዘንድ ለሚታየው መጥፎ ገጽታ አስተዋጽዖ እያበረከተ ቢሆንም፣ የወጣቱን ትውልድ ይነካል እና የወደፊት ህይወቱን ራዕይ ያሳጣዋል” ስትል ሰላም ተናግራለች።

በማኅበረሰብ ደረጃ ያለው ሌላው ዋነኛ መርዛማ ልምድ የኩዊር ቦታዎች ለሁሉም ኩዊር ሰው ክፍት አለምሆናቸው ነው። ትራንስ እና ባይሴክሽዋል ሰዎችን በኩዊር ማህበረሰቡ ውስጥ ያለማካተት ልምድ አለ። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ይህ አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች በአንዳንድ ማንነቶች እስከመጸየፍ ድረስ ይደርሳል። ይህ አንዳንድ ማንነቶችን አለመቀበል እና የኩዊር ቦታውችን ለሁሉም ኩዊር ሰው ክፍት አለማድረግ ማህበረሰቡ ለሁሉም ኩዊር ሰዎች ተቀባይነት እና ማበረታቻ ለመስጠት ያለውን ሃይል ይቀንሰዋል።

ነይላ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት እንደ ትልቅ ችግር ታየዋለች።

“ለምሳሌ በእድሜ ወይም ማንነታቸውን በመቀበል ረዘም ያለ ጊዜ የቆዩ ጥንዶች መሀከል ስለ ኩዊ ህይወታቸው ስትጠይቂያቸው መልሳቸው በሃዘን እና በመጥፎ አጋጣሚ የተሞላ ነው” ብላለች ነይላ።

በዚህ ረገድ አወንታዊ ልምዶች አለመኖራቸው ወጣት ኩዊር ሰዎች እራሳቸውን እንዳይቀበሉ እና የወደፊት ህይወታቸውን የበለጠ ትርጉም ያለው አድርገው እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል። አርአያነት የወጣቱ ኩዊር ትውልድ ራሱን መቀበል እንዲማር እና ውስጣዊ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነትን ለመቀየር እንዲሰራ ለማስቻል ወሳኝ ነው።

ሌላ ነይላ በኩዊር ማህበረሰቡ ዉስጥ ያለ ብላ የምታስበው ችግር አብዛኛዎቹ ትውውቆች ወደ ፍቅር ያመራሉ ተብለው መታሰባቸው



ነው። የጓደኝነትን አስፈላጊነት እና ማህበረሰቡን ለማስቀጠል የሚጫወተውን ሚና ቀጥላ አስረድታለች።

ሰላም በኩዊር ማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን መርዛማ ልምዶች ለማሻሻል ንግግርን እንደ አስፈላጊ መሳሪያ ለይታለች። ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ትርጉም ያለው ውይይት የሚካሄድባቸው የኩዊር ስብሰባዎች ቁልፍ ናቸው። ጥልቅ ግንዛቤን ለመጨመር የታቀዱ ሐቀኛ ንግግሮች ትምህርት ሊሰጡ እና ንቃተ-ህሊናን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።

“ዘጋቢ ፊልሞችን መመልከት እና ስለኩዊርነት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ስላሉትን የተለያዩ ማንነቶች ላይ ያለንን ግንዛቤ ማሳደግም መልካም ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል” ስትል ሰላም ተናግራለች።

በቀላሉ “ትንሿና ቀላሏ ልትደረግ ይገባል ብዬ የማስባት (ግን ደግሞ ከባድ የሆነብን) ነገር ለእኛ ያለነው እኛ መሆናችንን አውቀን እርስ በርስ መተሳሰብ እንዳለብን ማስገንዘብ መቻል ይመስለኛል” ብላለች ሰላም።



# በቡች እና ቡች መስህቦች ዙሪያው ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች

- ብስራት -

“በእርግጥ በሁለታችሁ መሃል ምንም ነገር እየተከናወነ አይመስለንም። ሁለት ወንዶች በአንድ ላይ እንደማለት እኮ ነው። ማን ይህንን ይፈልጋል?” የሚለው አስተያየት ሲሰነዘር ሞቅ ያለ ሳቅን አስነስቷል፤ ነገር ግን አምስት ኩዊር ሰዎች በተሰበሰቡበት መሃል አንዲት ኩዊር ሴት ይህንን ስትል ስሰማ በጣም ተገረምኩ።

ይህ አስተያየት የተሰጠው አንዲት ቡች (ወይንም በተለምዶ ወንዳወንድ ሴት) ሴት ስለ ሌላ ቡች ሴት እንደምትወዳት ግን ፍቅሯ እንደ “እህት” እንደሆነ ለቀለደችው ቀልድ ምላሽ ነው። የሚያስጨንቅ እና እንግዳ ነገር ሆኖብኛል። ሁለት ቡች ሴቶች የፍቅር ጓደኝነት እንዳይመሰርቱ የወሰነው ማን ነው? ሁለት ወንዶች የፍቅር ጓደኝነት እንዳይመሰርቱስ የሚወስነው ማነው? ማን ከማን ጋር ግንኙነት መፍጠር እንደሚችል የመወሰን ስልጣን ያለው ማነው? ከዚህም በላይ፣ ሁለት ራሳቸውን ቡች ብለው የተቀበሉ ሴቶች ዴት ለመደራረግ በመምርጣቸው ብቻ ወንድ ተብለው የሚሰየሙትስ ለምንድን ነው?

ምንም እንኳን እብሬ ባልስቅም እነዚህን ግርምቶች ባለመናገሬ እና ባለመቃወሜ በጣም ተፀፀቻለሁ። በራሳችን ማህበረሰብ ውስጥ እንደዚህ ያሉ አድሎአዊ ድርጊቶችን በመመርመር እና በመጋፈጥ የበለጠ ሁሉን አቀፍ አስተሳሰብና እና ግንዛቤን መፍጠር አስፈላጊ ነው።

- ሠላም -

እንደ እኔ ቡች ለቡች የፍቅር ግንኙነት በስፋት ጤናማ ነው ተብሎ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴት ማህበረሰብ ውስጥ አለመታሰቡ ያሳደረብኝ ተፅእኖ አለ። እኔ የምፈልጋቸዉ ሴቶች በተለምዶ ቡች በሚባሉት መሆናቸዉን በአጋጣሚ ስናገር የሚሰጡኝ አስተያየቶች እንዳሉ ሆነው  “እውነቷን ነው??” ብለው ለማመን ሲቸገሩ አያለሁ።

እኔ በግሌ እራሴ ላይ ይሄ በብዙዎቹ ዘንድ እንደ “ትአምር” ገፋ ሲልም እንደ “ነውር” የሚታየውን ፍላጎቴን ለመቀየር የማደርገው ጥረት አይኖርም ምክንያቱም መቀየር የምችለው ስላይደለ። ይልቅስ ለመቀየር መሰራት ያለበት እንደዚያ የሚያስቡት ሰዎች ጭንቅላት ላይ ይመስለኛል። ምክንያቱም ‘ፍቅር ፆታ የለውም’ ብሎ የሚያምን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ  ወርዶ “ፍቅርን ሱሪና ቀሚስ ለብሰው ካላየሁ ያመኛል” ሲሉ መስማት (የንዴት አይምሰልብኝ እንጂ) ነውርም፣ ድንቁርናም መሆኑ እስኪዋጥላቸው መንገር ያለብን ይመስለኛል!



# ጉዳትን መግለጥ፡ ቁልፍ ጉዳዮችን በ

1

## ኩዊር ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ስድብ

በፆታዊ ዝንባሌያቸው ላይ ተመስርተው ግለሰቦችን የሚያንቋሽሹ ቋንቋዎችን ወይም ስድቦችን መጠቀም፣ ጉዳቱን እና መድሎውን እንዲቀጥል ማድረግ።

2

## የትራንስ ጥላቻ የተሞላበት የተሳሳተ ጾታዊ ስያሜ

ሆን ተብሎ የተሳሳቱ ተውላጠ ስሞችን መጠቀም ወይም የግለሰቡን የተረጋገጠ የፆታ ማንነት እውቅና አለመስጠት፣ ልምዳቸውን ውድቅ ማድረግ።

3

## የሰውነት ማሸማቀቂያ አስተያየቶች

ስለ አንድ ሰው የሰውነት መጠን፣ ቅርፅ ወይም ገጽታ አሉታዊ ወይም ፍርደኛ አስተያየቶችን መስጠት፣ በሰውነት አቋም ደስታ ለማጣት  እና ለራስ ክብር ዝቅተኛነት አስተዋፅዖ ያደርጋል።

4

## አግላይ ቋንቋ

በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የተወሰኑ ማንነቶችን የሚያገለል ወይም የሚያጠፋ ቋንቋ መጠቀም፣ ማግለልና መከፋፈልን ማጠናከር።

5

## ሳይበር ጉልበተኝነት እና ዶክሲንግ

በኦንላይን ትንኮሳ ውስጥ መሳተፍ፣ ወሬ ማሰራጨት፣ ያለፈቃድ የግል መረጃን ማጋራት፣ ወይም በግላዊ ጥቃቶች እና ዛቻዎች በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ መሳተፍ፣ ስሜታዊ ጉዳት ማስከተል።

# ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ መፍታት

6

## ባይሴክሿልነትን መደምሰስ

ባይሴክሿልነትን ወይም  ሌላ ነጠላ ያልሆኑ ማንነቶችን መኖር እና መካድ፣ ልምዶቻቸውን ማጥፋት እና መገለልን ማስቀጠል።

7

## ብሄር ተኮር እና የጎሳ ጥቃቅን ጥቃት

አፀያፊ አስተያየቶችን መስጠት ወይም በግለሰቦች ላይ በብሄር ወይም በጎሳ ላይ የተመሰረተ አድሎአዊ ድርጊቶችን መፈፀም፣ የስርአት ጭቆና እንዲቀጥል ማድረግ።

8

## ሄትሮኖርማቲቪ ግምቶች

በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው የተለያየ የፆታ እና የፆታ አገላለጾችን ችላ በማለት ከታቃራኒ ፆታ አፍቃሪዎች ፍላጎቶች ጋር የሚስማማ መሆኑን ማሰብ።

9

## የአጋርነት እጦት

በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የተገለሉ ግለሰቦችን መደገፍ እና አብሮ መቆም አለመቻል፣ የግዴለሽነት ባህልን ማስቀጠል።

10

## የቦታ ከልካዮች

ጥብቅ መመዘኛዎችን መጫን ወይም በኩዊር ቦታዎች ማን እንደተፈቀደለት ወይም እንደተቀበለ፣ የተወሰኑ ነገሮችን አያሞሉም ተብለው የታሰቡ ሰዎችን ማግለል።

# ከመርዛማነቱ ማምለጥ፡
# የመዳን እና ራስን የማሰብ ጉዞ





አንድ ጊዜማ
ጭራሽኑ በቢላ
ልታስፈራራት
ሞክራለች።

ሁለት አመት የቆየ ግንኙነት ነበረን። የሚያሳዝነው ግን ከነዚህ ረጅም ሁለት ዓመታት ውስጥ አንድ ዓመት ተኩሉን ገሃነም ውስጥ መኖር በሚመስል ሁኔታ ማሳለፌ ነው። ጠዋት ማታ ንትርክ ነው። በረባ ባልረባው ጭቅጭቅ ነው። ፊቴ በነጋ ጠባ ለቅሶ እስኪያብጥ ድረስ ሰላም የሚባል ነገር የለኝም። የማልረሳቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ቀኑን ሙሉ ስራ ውዬ አምሽቼ ቤት እንደገባሁ ሌሊት ሙሉ ስልክ እንዳወራ እገደዳለሁ፤ ወሬው ስለ ፍቅር ወይንም ስለ ወደፊት እቅዶቻችን ቢሆን ደግሞ ደስ ባለኝ። ነገር ግን እንትን አደረግሽ ፣ እንትና ጋር አወራሽ እያለች ለሊቱን ሙሉ ታስለቅሰኝና በጠዋት እንዲሁ ሳልተኛ ስራ እገባለሁ።

የዚህ ሁሉ መንስኤ የድሮ የፍቅር ጓደኛዬ ነበረች። በጣም ሃይለኛ እና መርዛማ ባህሪ ነው የነበራት። ሁሌ እኔን በጉልበት ለማያዝ ትፈልጋለች። ከማንም ዓይነት ሰው ጋር እንድገናኝ ወይንም እንዳወራ አትፈልግም። በአላፊው በአግዳሚው ትጠረጥረኛለች እናም ሌላ ነገር አለሽ እያለች ታስቸግረኛለች። አንድ ጊዜማ ጭራሽኑ በቢላ ልታስፈራራኝ ሞክራለች።

በርግጥ ግንኙነታችን ለህይወቴ የሚያስጋ ቢሆንም ከዛሬ ነገ ትሻሻላለች በሚል ተስፋ አብሬያት ቆየሁ። ነገርግን ከሷ ባህሪ ጋር ለመኖር ብዙ ግዜ እታገል ነበር። እሷን ላለማስቀየም፣ ላለማጣት መሆን የሌለብኝን ሁሉ እየሆንኩኝ ለረጅም ጊዜ ቀጠልን። ስለምወዳትም ወደኔ መስመር አመጣታለሁ ብዬ ነበር የማስበው። እንደውም የሷ ለከት ማጣት ምናልባት የአይምሮ የጤና እክል ይሆናል ብዬ እንዳስብ አድርጎኝ ነበር። ጤናማ ብትሆን እንደዚህ እየወደድኳት እና እንደዚህ ዋጋ እየከፈልኩላት፤ በፍቅር አብረን ለመኖር ይህን ሁሉ ነገር እያደረኩኝ ትረዳኝ ነበር ብዬ አስብ ነበር። ይህንንም በማሰብ ካለሁበት አገር በየሶስት ወሩ እሷን ለማየት እመላለስ ነበረ። ግን ምን ያደርጋል ከአንድ ቀን በላይ ሰላም እና ፍቅር ያለው ጊዜ አብረን አናሳልፍም፤ ያው እንደተለመደው ሁለተኛው ቀን ላይ ምክንያት ፈልጋ ጥል ውስጥ ትገባና ምንም ደስታ የሌለው ሁኔታ ውስጥ ትከተናለች። ይህም ቢሆን ግን ሁኔታዎች ከዛሬ ነገ ይሻላሉ እያልኩኝ እኔም መሄዱን አላቋረጥኩኝም፤ እሷም ነገሯን አላቋረጠችም። እንደዚህም ሆኖ ግን እኔ ከሷ ጋር ለመኖር እማወጣቸው እቅዶች እንደቀጠሉ ነበሩ።

እኔ በፍቅር እንደቀረብኳት እሷም በፍቅር ነው የቀረበችኝ ብዬ ስለማምን ብዙ መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ነበርኩ። ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ካልተደረገ የምትለው ነገር እየባሰ መጣ። ለምሳሌ ስለ አብሮ መኖር ሲወራ እኔ አሁን አብረን ከመኖር ይልቅ እቅድ ብናወጣ እና ብንዘጋጅ ይሻላል ያልኩትን ሐሳብ እንደ አንድ ክፉ የማስረጃ ነጥብ ይዛ በሌላ ጊዜ ዛሬውኑ ከኔጋ ካልኖርሽ እንደዚህ አደርጋለሁ ብላ ወደ ክፋት የሆነ ነገር ትሄዳለች። በርግጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ወይንም ሶስት ወር ምንም ስጋት አልነበረኝም ከዛ ወዲያ ግን የቀረውን በተለይም አንድ አመት ከስድስት ወር ጊዜ በጣም በትልቅ ስጋት እና ጭንቀት ነው ያሳለፍኩ። በትክክል አብሬ መሆን ፈልጌ ሳይሆን በፍራቻ ነበር አብሬያት የነበርኩት።

ነገር ግን በቃኝ ከዚህ ወዲህ ከአንቺ ጋር መሆን አልፈልግም ወደ ማለት ስመጣ ማስፈራራት ትጀምራለች። እኔም አሁን ከአሁን አሁን ቤተሰቤ ጋር ስልክ ደውላ ትናገራለች በሚል ስጋት እዋጣለሁ። በደጉ ጊዜ ቤተሰቤን ስላስተዋወኳት አንድ ሰው ጋር ደውላ “እሷ እኮ እንደዚህ ናት” ብላ ብታወራ አለቀልኝ ማለት ነው። ምክንያቱም በጣም ጓደኛዬ እንደሆነች ስለተናገርኩኝ የምትላቸውን ለማመን በጣም ቅርብ ናቸው፤ በነሱ ዐይን መግቢያ መውጫዬን የምታውቅ እና ታማኝነት ያላት ሰው ናት። አንዳንዴ እንዴት ብዬ እንደምለያይ ግራ ይገባኛል። ምን አይነት ነገር ውስጥ እንደገባሁኝ ሳስብ ይጨልምብኛል። ቢጨንቀኝ ለመለያየት ስል “እኔኮ ሴት አልወድም እላታለሁ” ፤ የማልቀባጥረው ነገር አልነበረም። አዝማማዬን እያየች ማስፈራራቱን ቀጠለች።

በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ ቢከብደኝም መውጫ መንገዱ ግን ግራ ገባኝ። በጭንቀት መወጠር የእለት ተእለት እጣ ፋንታዬ ሆነ። ታዲያ አንድ ቀን ይህንኑ እያብሰለሰልኩ ሳላስበው ወደፊት እየነዳሁኝ መስሎኝ መኪናውን ወደ ኋላሁት ነዳሁት እና ሄጄ ከኤሌክትሪክ ምሰሶ ጋር ተላተምኩኝ። በዚህ ተደናግጬ ሳይወጣልኝ የመጨረሻ መጥፎ የመኪና አደጋ ድጋሚ ደረሰብኝ። መሄድ እያለብኝ እኔ ግን ልቤ ጠፍቶ መሃል መንገድ ላይ ዝም ብዬ ቆሜያለሁ፤ ምንም ድምጽ እየሰማሁም አይደለም ምክያቱም ቀልቤ ከኔ ጋር የለም። መጨረሻ በፍጥነት የመጣ መኪና ወጣብኝ። ክፉ አደጋ ነበር፤ እንደውም እግዚአብሔር በሚያወጣኝ አወጣኝ ብዬ ነው የማስበው። በጊዜው አደጋው ክፉ ቢሆንም ለራሴ ቆም ብዬ እንዳስብ ግን እድል ሰጥኝ። የመኪና አደጋው በገሃድ ያሳየኝ ጭንቀቴ ምን ያህል ጥግ እንደሄደ ነበር፤ ስለዚህም እራሴን ማረጋጋት እና የመጣው ይምጣ ወደሚለው ነገር እንድሄድ አደረገኝ ምክያቱም በጭንቀት የተነሳ ሞትም እንዳለ ማሰብ ጀምርኩኝ። ምንም ነገር ከሞት አይበልጥም፣ ከመሞት ብናገር

ይሻላል ብዬ ለራሴ ወሰንኩኝ።


ውሳኔዬን ስነግራት ደስተኛ አልነበረችም። እንደተለመደው ስታስፈራራኝ እና ስትዝትብኝ ከዚህ በላይ አልችልም ብዬ ውሳኔዬን ነግሬያት ከሁሉም ፔጆቼ ላይ ብሎክ አደረኳት። ያኔ በደህና ጊዜ እረፍት ስንወጣ ከተነሳነው ቪዲዮ አንዱን ቪዲዮ ለጓደኛዬ ላከችላት። ጓደኛዬ ሌዝቢያን ነበረችና ቪዲዮን ወደኔ ከላከችልኝ በሀላ “ይሄንን ቪድዮ ወደ እኔ ከላከች ለሌላ ሰው እንደማትልከው ምን ዋስትና አለሽ?” አለችኝ። ፍርሃት እና ጭንቀት በቅትውኝ ነበር ስለዚህም “የፈለግሽውን አድርጊ” አልኳት። “ተናገሪ ችግር የለውም፤ አንቺ ፍንጭ ከሰጠሻቸው የቀረውን እኔ በደንብ አስረድቼ ጨርሼ እነግራችኋለሁ” አልኳት ። ቤተሰቦቼ በጣም ወግ አጥባቂ ስለሆኑ ለሚደርሰብኝን ነገር ራሴን ማዘጋጀት ጀመርኩኝ። በእርግጠኝነት ከቤት ያስወጡኛል ግን እኔ በራሴ መኖር እጀምራለሁ ወደሚለው ሐሳብ ስመጣ የሷ ማስፈራራት ውሳኔዬን እንደማያስቀይረኝ ስለገባት ማስፈራራቱን አቆመች።


ህይወቴ ከሷ ጋር ለመለያየት ድፍረት አግኝቼ ከዛሬ አምስት ወር በፊት እስከተዋት ድረስ የምድር ሲኦል ነበር። ራሴን ያለመሆን ደረጃ ደርሻለሁ፤ ቤተሰቦቼ በጣም ታታሪ እና በጣም ከፍ አድርገው የሚያስቡኝ ልጅ ብሆንም የሆነ ሰዓት ላይ ግን የጭንቅላት ሽከሙ ብሶብኝ መሪዬን ይጌ ሁሉን ነገር እስከ መርሳት ድረስ ደረሻለሁኝ። የወደድኩት ሰዉ በዚህ ደረጃ ከፋት እንዴት ያስባል ብዬ በጣም እጨነቅ ነበር። በምትወጂው ሰው መካድ በጣም ከባድ ነው። ከዚህ በኋላስ የኔ ብዬ ሰው የምቀርበው እንዴት ነው ብዬ እጨነቅ ነበር። አሁን ሳስበው ግን ገላገለችኝ ነው የምለው።

ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው የፍቅር ግንኙነቴ መጥፎ ይሆናል ብዬ እራሴን አላሳምነውም። ግን አሁን ከአንድ ሰው ጋር ግንኙነት ከመጀመሬ በፊት ስለ እዛ ሰው በትክክል ብዙ ነገሮችን ማወቅ፣ የብስለት ደረጃቸው ከኔ ጋር እንደምሄድ እና ከባድ አጋጣሚዎችን እንዴት ይወጣሉ የሚሉትን ነገሮች መጀመሪያ ማየት እና ማወቅ እፈልጋለሁ። እንደ በፊቱ “ፎንቃ” ነው ብዬ ዘልዬ መግባት አልፈልግም። ብፈልግም ይህንን የምችልበት አይመስለኝም ምክንያቱም ያሳለፍኩት ጊዜ በቂ ትምህርት ነው። ዛሬ ምንም አይነት ግንኙነት ከመጀመሪያ በፊት ራሴ ላይ መስራት ነው የምፈልገው። በኢኮኖሚ እራሴን ጠንካራ እማደርግበትን መንገዶች ነው የምፈለገው፤ ራሴን በራሴ ለማቆም በጣም ብዙ እሞክራለሁ እታገላለሁ በማንም ሰው ስር መገኘት አልፈልግም።

## እንደ በፊቱ “ፎንቃ” ነው ብዬ ዘልዬ መግባት አልፈልግም።

# አካልን የማሸማቀቅ ድርጊቶች እና ራስን መውደድን መማር





ከሆነ ጊዜ በፊት እኔ እና ፍቅረኛዬ ከሌላ ጥንዶች ጋር ደብል ዴት ወጣን። አብረውን የነበሩት ካፕል ሲያስቀኑ! ይስቃሉ፣ ይጫወታሉ፣ አንዷ ሌላኛዋን ወደላይ ብድግ እያደረገች ታቅፋታለች፣ ትሸከማታለች። እነሱ በተቃቀፉ እና በተሸካከሙ ቁጥር የኔ ፍቅረኛ ዞር ዞር እያለች አይን አይኔን ታየኛለች። የኔ ሰውነት ሞላ ያለ ስለነበር ፍቅረኛዬ እኔን ዛሬ እንዳየችው ማገላበጥ አትችልም። ዞራ ባየቺኝ ቁጥር እኔ ደግሞ ተሳቅቄ ልሞት! ቀጠልም አድርጋ “አንቺ ግን ለምንድነው ስፖርት የማትሰሪው? እኛም እንደዚህ አይነት ጊዜ እንድናሳልፍ መከሳት አለብሽ!” ብላኝ እርፍ! ምነው! እንደዚህ አይነት ፍቅር ጥንቅር ብሎ ቢቀርስ?

ይህ ሰዎች በሰውነቴ ሊያሳፍሩኝ ወይም ሊያሸማቅቁኝ የሞከሩበት ብቸኛ አጋጣሚ ቢሆን በምን እድሌ። ያኔ በራስ መተማመን ብዙም አልነበረኝም። አንድን ሴት እንኳን ተዋውቄ ገና ልንገናኝ ስናስብ ጭንቀት ይለቅብኛል። እሷ እኔ ምን ልመስል እንደምችል በምናቧ የሳለችውን ምስል ላልመስል ስለምችል ትጠላኛለች በሚል አስተሳሰብ እምላለሁ። አንድ ሴታሴት ልጅ ቅርጿ የሚያምር፣ ወገቧ ቀጠን ብሎ ዳሌዋ የሰፋ፣ ከንፈሯ ቅርጽ ያለው፣ አይኗ ጎላ ያለ፣ ጥፍር እና ፀጉራን በየጊዜው የምትሰራ፣ እነደው ቅብጥ ያለች መሆን አለባት የሚለውን አስተሳሰብ ስለተቀበልኩኝ በራሴ ሰውነት እና አኳኋን አፍርና እሸማቀቅ ነበር። የማገኛት ልጅ ገና ስታየኝ ትጠላኛለች ብዬም እራሴን ስለማሳምነው ጭራሽ ለመዋብም ሆነ ለማጌጥ ምንም አይነት ሙከራ አላደርግም ነበር። ይህ ፍራቻዬም በከንቱ አልነበረም። አንዳንዶቹ ምንም ባይናገሩም ገና ሲያዩኝ ፊታቸው ይቀያየራል። አንዳንዶቹ ደግሞ እዛው ፊቴ “የጠበኩት እንደዚህ አይነት ሰው አልነበረም” ብለው ይነግሩኛል። ከነሱ የተረፉት ደግሞ ስለእኔ ያሉት ነገር በሰው በሰው ዞሮ ይደርሰኛል። “ምን እንደምታክል እኮ? ማን ነኝ ብላ ነው የምትኮራው?” ይሉኛል።

በኛ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ ለንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች መንገድ የሚከፍተው የምንተዋወቅበት መንገድ ነው ብዬ አስባለሁ። አብዛኛውን ጊዜ ገና ከመጀመሪያው በአካል መተዋወቅ ስለማንችል በማህበረሰባዊ ድህረ ገጾች ማንነታችንን ሸፍነን ነው የምንተዋወቀው። ከዛም ፎቶ ከመላላካችን ወይም በአካል ከመተያየታችን በፊት እርስ በርስ መተማመን ስላለብን በደንብ የምንግባባው በጽሁፍ ነው። ስለብዙም ነገር እናወራለን፣ እንግባባለን። እናም አንዳንዶቻችን ከመተያየታችን በፊት በአስተሳሰባችን እና በአወራራችን ብቻ ጠፍ ያለ ፍቅር ሊይዘን ይችላል። ስለዚህ ሰው ከምናውቀው ተነስተን ይህን ይመስላሉ ብለንም የምናስበው ነገር ይፈጠራል። እኔ ተግባቢ ወይም የምረዳ ሰው ስለሆንኩኝ ግን ሞዴል እመስላለሁ ማለት አይደለም። እናም ስንገናኝ ስለኔ አስባ ከመጣችው ምስል ጋር ስላልተመሳሰልኩ እኔን ደግማ ማየት ወይም ማናገር አትፈልግም። ይህንን ፍራቻ ይዞ ስንቱ ሰው ነው የሌላ ሰው ፎቶ በመጠቀም ከሰው ጋር የሚያወራው? እስካሁን ስትግባቢያት፣ አብረሻት ስትስቂ እና ስለሁሉ ነገራችው ስታወሩ ከከረማችሁት ሴት ጋር ተገናኝተሽ አሪፍ ነገር እንቀጥላለን ብለሽ ስታስቢ ግን ይቺ ሴት ከዛ በኋላ ድምጿን አጥፍታ ስትጠፋ በጣም ስሜት ይሰብራል። የሆነ ነገር እንደጎደለሽ እና ብቁ እንዳልሆንሽ ይሰማሻል።

ይህ አስተሳሰብ ደግሞ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴቶች ላይ መባሱ ይገርማል። የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪያን መሃከል እሱና እሷ ነገሮችን በተመሳሳይ መንገድ ስለማይረዱ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ቢፈጠር እኔም ብዙ አይገርመኝም። ነገር ግን ሁለታችንም ሴቶች ሆነን፣ ይህ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚያየን እያወቅን፣ ማንነታችንን ለራሳችን ለመቀበል ያለውን ውጣ ውረድ እያየን እንዴት አልፈን ሌላ ሰውን በሰውነቷ ልንሳደብ ወይም ልናሳፍራት እንሞክራለን?

የውፍረት እና የቅጥነት ጉዳይ ብቻ አይደለም። በኛ ማህበረሰብ ውስጥ አንድ “ሴታ ሴት” ወይም “ወንዳ ወንድ” ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ እንዴት መልበስ፣ ማውራት እና መሆን እንዳለባት ቀድመን መስፈርት አስቀምጠናል። ከዛ መስፈርት ወጣ ያሉ ሰዎችን ስናገኝ ተጠቋቁመን ለማሳፈር እንሞክራለን። “ወንዳወንድ ሆና እንዴት ዳሌ እና ቂጥ ይኖራታል? እንዴትስ ጡቶቿ ከቲሸርቷ ላይ ይታያሉ?” ብለን እናማለን። የመረጠችው የአለባበስ እና የአኳኋን ዘይቤ በተለምዶ “የወንድ” ቢባልም ሴትነቷን ግን አልቀየረችም። እና ሰውነቷን ወዴት ታድርገው? አንዷ የቅርብ ጓደኞችን ብዙ ጊዜ በዚህ ጉዳይ አፍ ዉስጥ ትገባለች። አብዛኛውን ጊዜ የወንዳወንድ አለባበስ ስላላት ለተለያየ ጉዳይ ለምሳሌ ወደቤተክርስትያን ስትሄድ ቀሚስ ስትለብስ የኛ ማህበረሰብ ይጠቋቆምባታል። “እረ እቺ እኮ ሴታሴት ናት ‘ስታድ’ [ወንዳወንድ] አይደለችም” ይላሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያንን ከሃይማኖታችን እና ከባህላችን የወጣ ነው ብለው ማንነታችንን ይገድቡናል፣ ያገሉናል። እኛም ይባስ ብለን እርስ በርሳችን በሰውነት ወይም በፆታ አገላለጻችን ለመገዳደብ እንሞክራለን።

ሰውነት የማሸማቀቁ ልምድ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ በጣም ከምናምናቸው ሰዎች ጋር እንኳን ሙሉ ለሙሉ ምቾት አይሰማንም። አንዳንዴ ጊዜ ያሳልፍንባቸው የፍቅር ግንኙነቶች ሳይሳኩ ሲቀሩ፣ የፍቅር ጓደኞቻችን ለኛ ምንም

**ሰውነት የማሸማቀቁ ልምድ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ በጣም ከምናምናቸው ሰዎች ጋር እንኳን ሙሉ ለሙሉ ምቾት አይሰማንም።**


አስተሳሰብ በሌለው መንገር ዞር ብለው ስለእኛ ሰውነት “እንደዚህ ናት፣ እንደዚህ ትወዳለች፣ ሰውነቷ ላይ እንደዚህ አለባት” እያሉ ያወራሉ። ሰውነትን ከሌላ ሰው ጋር መጋራት ብዙ እምነትን ይጠይቃል። እናም ግንኙነቱ ስላልዘለቀ ዞሮ መዋጋት አስፈላጊ ነው ብዬ አላስብም።

እንደዚህ አይነት ነገር ሳይ እኔም ዝም አልልም፤ ወጥሬ ነው የምከራከረው። ሰው መመዘን ያለበት በአስተሳሰቡ እና በድርጊቱ ነው እንጂ በሰውነቱ መሆን የለበትም። ሁላችንም የተለያየ ሰውነት አለን፤ አጭር ወይም ረጅም፣ ቀጭን ወይም ወፍራም፣ ቀይ ወይም ጠይም ብንሆንም ሁላችንም እናምራለን። ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴት ለመሆንም አንድ መንገድ ብቻ አይደለም ያለው። ሁላችንም እስከተመቸን ድረስ በፈለግነው መንገድ እራሳችንን መግለፅ መቻል አለብን። እርስ በርስም የተለያዩ አይነት አገላለፆችን ለመቀበል አስተሳሰባችንን ክፍት ማድረግ መቻል አለብን።

እኔ ዛሬ ላይ ሰው ስለኔ ሰውነት የፈለገውን ቢል ምንም አይመስለኝም። ምክንያቱም የራስ-ፍቅር ስላዳበርኩኝ ነው። ዛሬ ላይ ያለኝ እውቀት የዛሬ ስንት ዓመት ከነበረኝ ጋር አንድ አይደለም። አሁን ሰውነቴን እወደዋለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን አሁን አስተሳሰቤ ስለተቀየረ ባለኝ አቋም አሳምረዋለሁ። እኔን የተሰማኝ ነፃነት ለሁሉም ሰው እንዲሰማው ስለምፈልግ እስከጥግ ድረስ ሄጄ እከራከራለሁ።

# ዝምታውን መስበር: ከሁለትዮሽ ፆታ ውጭ የሆኑ ግለሰቦች ላይ ጥላቻን መቃወም





… ተውላጠ
ስሜን ሆን
ብሎ ማሳሳት፤
በተደጋጋሚ
“አንቺ” ነኝ
ብዬ ብናገርም
አለመቀበል
እና ጭቅጭቅ
መፍጠር
አጋጥሞኛል።



**እኔም በግሌ ብዙ አይነት ጥላቻዎች አጋጥሞኛል። በማህበራዊ ሚዲያው ብቻ ሳይሆን በአካልም እንዲሁ ከእኛው ማህበረሰብ ጥላቻ አጋጥሞኛል።**

ማህበራዊ ሚዲያን የተቀላቀልኩት በጣም ከብዙ አመት በፊት ነው። ከኔ በፊት ብዙዎች ቢኖሩም ከስምንት አመት በፊት ነው ወደዚህ የመጣሁት። በዛን ወቅት ስለማንነቴ እንዳውቅ ያገዘኝ ሰው ነው ወደማህበራዊ ሚዲያ ያቀላቀለኝ። እሱ ቀድሞ በዛ መንገድ ማህበረሰቡን ያገኝ ስለነበር እኔም እንዴት ሌሎችን ማግኘት እንደምችል ባሳየኝ መሰረት ነው የተቀላቀልኩት። በዛን ጊዜ በደንብ የሚታወቀው ፌስቡክ ነበር። የመንግስት ስሜን ሳልፅፍ ይገልፀኛል ባልኩበት ስም አካውንት ከፍቼ፣ ፎቶም የፊት ገፅታዬን ሳላሳይ እና ድብቅ የሆነ ፎቶ ፕሮፋይል በማድረግ ከሰዎች ጋር በዛ መንገድ ነበር መተዋወቅ እና መገናኘት የጀመርኩት።

ማህበራዊ ሚዲያን ለተለያዩ ነገሮች ልናውል እንችላለን፤ ለመጥፎም ለጥሩም። እንደሃገር የፍቅር እና የመከባበር ባህል ያለበት እንላለን እንጂ በጣም ብዙ በጥላቻ ላይ የተመሰረቱ አመለካከቶች የሚንፀባረቁበት ሃገር ነው። የሰዎች ማንነት ላይ አስተያየት መስጠት የሚያበዛ ማህብረሰብ ነው ኢትዮጵያዊ። ኢትዮጵያዊነቴን እወደዋለሁ፤ ያኮራኛልም። ነገር ግን እውነታውን ደግሞ መደበቅ አልፈልግም። በሰዎች የሰውነት ቅርፅ ላይ ማለትም በውፍረት እና በቅጥነት ላይ ያልተጠየቀ አስተያየት እንሰጣለን ፣ ሰዎች ላይ በጅምላ እንፈርዳለን ፣ በምርጫ የሚደረግ ነገር ላይ እንፈርዳለን (ለምሳሌ ከፀጉር ስታይላቸው ተነስተን ራስታ ሰዎችን እንደዱሪዬ እንቆጥራለን) ፣ በህዝብ ቁጥር ብዛት ትንሽ የሆኑ ብሄሮች ላይ እናፌዛለን እና ከፖለቲካ ድጋፍ የተገለሉ ማህበረሰብን በጅምላ እናጠቃለን፤ ብቻ ብዙ ብዙ የማህበራዊ ሚዲያ ጥላቻ ይደረጋል።

ምንም እንኳን በሕብረተሰቡ የተገለልን ብንሆንም እኛም ይሄንኑ እያየን ስለመጣን እና ስላደግን ይመስለኛል ከዚህ የተሻለ ነገር አናሳይም። እኛ የምንፈልገውን እና የለመድነውን ብቻ ማየት እንጂ ከዛ ውጪ ለመቀበል ዝግጁ አይደለንም። ለምሳሌ ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የተለየ አለባበስ የሚያስደስታቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ እነዛ ሰዎች ላይ ማፌዝ፣ በሰውነት ክብደታቸው “መደበኛ” ከምንለው ወጣ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በእድሜ የገፉ ኩዊር ሰዎች እና የመሳሰሉትን በአንድም ሆነ በሌላ የማግለል ነገር ይኖራል። የኩዊር ማህበረሰብ የተለያዩ ወስባዊ እና ስርዓተ ፆታዊ ማንነቶችን የያዘ ማህበረሰብ ነው። የጾታ ሁለትዮሽን የማይቀበሉ (non binary) ሆነው ጌይ ፣ ክሮስድሬሰር እንዲሁም ደግሞ ፆታቸውን የቀየሩ (transgender) የሆኑ የተለይዩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ላይ ደግሞ የሚደርሰው ጥላቻ ቀላል የሚባል አይደለም። የራስ መተማመናቸውን፣ የራስ ፍቅር እና ክብር ሁሉ ለመጉዳት የሚደረግ ጥላቻ በእኛው ማህበረሰብ በስፋት አለ። የማንቋሸሽ እና ሴታሴትነትን እንደስድብ መውሰድ በጣም ይታያል። ይህ አይነቱ ጥላቻ ብዙውችን ለድብርት እንዳጋለጣቸው አውቃለሁ። ራስን እስከማጥፋት ሊዳርግ እንደሚችልም አልጠራጠርም።

እኔም በግሌ ብዙ አይነት ጥላቻዎች አጋጥሞኛል። በማህበራዊ ሚዲያው ብቻ ሳይሆን በአካልም እንዲሁ ከእኛው ማህበረሰብ ጥላቻ አጋጥሞኛል። እኔ በስርዓተ ፃታ አገላለፄ በተለምዶ “ሴታሴት” ወደሚለው አዘነብላለሁ እና በተለያየ ጊዜ “እኔ ወንድ እንጂ ለሴታሴትማ ሴት ጋር አልሄድም እንዴ?” የሚሉ ብዙ ገጥመውኛል። ወይ ደግሞ ተውላጠ ስሜን ሆን ብሎ ማሳሳት፤ በተደጋጋሚ “አንቺ” ነኝ ብዬ ብናገርም አለመቀበል እና ጭቅጭቅ መፍጠር አጋጥሞኛል። ምንም እንኳን ሁሉም ሰው በእኔ ተማርኮ እንዲኖረው ባልጠብቅም ከማህበረሰቡ ግን ሁሉም ሰው እንዲያከብረኝ እና እኔን ዝቅ እንዳያደርገኝ እጠብቃለሁ። ያየኝ ሁሉ ያፍቅረኝ ወይም ወሲባዊ ፍላጎት ይኑረው የሚል አመለካከት የለኝም ነገር ግን የኩዊር ማህበረሰቡ ገና ሲያዩኝ የሚሰጡኝ ፍርድ አግባብ አይደለም። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚደረገውንም ማሾፍ ልክ አይደለም


ብዬ ስከራከር ወይም ለማስረዳት ስሞክር “ቀልድ እኮ ነው ለምን ገገማ ትሆናላችሁ?” የሚል ምላሽ ይኖራል። ለምን በዚህ ነገር ይቀለዳል?

መጠላትን እና መገለል የሚፈልግ ሰው የለም፤ ሁሉም ሰው መከበርን ይፈልጋል። ጥላቻን ማስተናገድ የሚፈጥረውን ስሜት ለመግለፅ ይከብደኛል። አንዳንዴ እንደቀልድ ብለው የለጠፉትን ፖስት በአጋጣሚ አይቼ ቀኑን ሙሉ በአዕምሮዬ እየተመላለሰ ሲረብሸኝ እና ሲያበሳጨኝ ይውላል። ይበልጥ ነገሩን የሚያከብደው ደግሞ ማህበረሰቤ ነው። እኔን ይወክለኛል ከምለው ማህበረሰብ የሚሰነዘር ጥላቻ መሆኑ ነው።


በጣም ብዙ ጥላቻን እንዳስተናገድኩ እንደ አንድ የጾታ ሁለትዮሽን የማይቀበል ኩዊር ሰው ራሴን የምነግረው ነገር የምቀየር ሰው እንዳልሆንኩ ነው። ራሴን ተቀብዬዋለሁ፤ ወድጄዋለሁ። ከኩዊር ማህበረሰቡም ሆነ ከሌላ ጫናዎቹን እንድቋቋም የረዳኝ ለራሴ ያለኝን አመለካከት መገንባቴ ይመስለኛል። አንዳድ ጥላቻዎች ደግሞ ከፍርሃት የመነጬ መሆናቸውንም ለመረዳት እሞክራለሁ። ያለንበት ሃገር እንደፈለግን ለመንቀሳቀስ አይፈቅድልም ማለትም ሴታሴት ሆኜ እንደፈለኩ ከሌላ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሰው ጋር መንቀሳቀስ አልችልም ስለዚህ ሌሎች ሰዎች ከእኔ ጋር ወይም መሰሎቼ ጋር መታየትን ስለሚፈሩ መገናኘቱን አይፈልጉትም። እዚህ ላይ ደግሞ ለመምከር ያህል እኛም ጥንቃቄ ያስፈልገናል። ራሳችንን መካድ ሳይሆን አገላለፃችንን ከቦታ እና ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም በብልጠት መንቀሳቀስ ያስፈልገናል። ነገር ግን አብዛኛውን ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ጭፍን ጥላቻ እንዳለባቸው አውቃለሁ። “ወንድ ከሆነ እንደወንድ ይሁን ሴት ከሆነች እንደሴት ትሁን” ወይም “ስርዓተ ፆታ ወንድ እና ሴት ብቻ ነው” ብለው ከሃይማኖት ወይም ከባህል ጋር በማያያዝ የሚጠሉን የእኛው ማህበረሰብ አባላት ቁጥር ትንሽ አይደለም። እነዚህን አይነቱን ሰዎችን በመራቅ እና የሚለጥፉትን ባለማየት ነው የአዕምሮ ጤናዬን የምጠብቀው። ተናግሬ የማልቀይራቸው ሰዎች ስለሆኑ መተው ነው።


ይሄን ሁሉ ስል ግን ማህበረሰባችን ላይ ያለውን መርዛማ ልምድ ብቻ ማንሳት ወደኋላ ይጎትተናል ለማለት እንጂ በእኛው ማህበረሰብ በጣም ብዙ የሰውን መብት እና ምርጫ የሚያከብሩ እንዳሉ ማስታወስ እፈልጋለሁ። የሚያበረቱንን የሚደግፉንን ፈጣሪ ያብዛልን ምክንያቱም በጣም ያስፈልጉናል።

መልካም አመለካከት እንዲኖረን እመኛለሁ!



# በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ አሉባልታዎችን፣ ወሬዎችን እና መርዛማነትን መፍታት





የድሮ ፍቅረኛዬ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለ እኔ ወሬ ማሰራጨት ጀመረች። መጀመሪያ ላይ ብዙም ባይረብሸኝም ወሬው የተጓዘበት ፍጥነት የሚያያስብ ነበር።

በድሮ ፍቅረኛዬ እና በእኔ መካከል ለተፈጠረው ችግር ትልቁ ምክንያት የጓደኞቿ ብዛት ነው። በመካከላችን ችግር በተፈጠረ ቁጥር ለጥቂት ቀናት ከቤት ትወጣለች፤ እና እሷ በሌለችበት ቀናቶች ከጓደኞቿ የተለያዩ ስድቦች እና ወቀሳዎች ይደርስብኛል።

ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ስታደርግ ይቅር ማለት አልነበረብኝም ምክንያቱም ይቅር ያልኳት ጊዜያት ሁሉ ክብርን ማጣትን አስከትሏል። በእውነቱ ጓደኞቿን አልወቅስም። ካላከበረችኝ ጓደኞቿ እንዴት ያከብሩኛል? በተመሳሳይ ሁኔታ እነሱም ጣልቃ መግባት አልነበረባቸውም። በእኔና በሷ መካከል እየነደደ ባለው እሳት ላይ ቤንዚን ደጋግመው ጨመሩ። ከጣልቃ ገብነት በተጨማሪ እሷ የነዛችውን አሉባልታ በማሰራጨት ረገድ አስተዋፅዖ አበርክተዋል።

እንደ እድል ሆኖ፣ ስለ ሐሜት ብዙም ግድ የለኝም፣ እናም ሰዎች ስለ እኔ ያላቸው አመለካከት ወይም ስለ እኔ ለሚሉት ነገር ግድ የለኝም። ለዚህ በረከትም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እንደዛ ባልሆን ኖሮ በተናገሩት ነገር እጎደብ ነበር፡ ስለኔ ስለተወራው ወሬ በዝርዝር መናገር ባልችልም እኔን ለመስበር ስልጣን ነበራቸው።

ይህ ሁሉ ሆኖ በመካከላችን ያለውን ችግር ለመፍታት በሚቻልበት መንገድ ለመወያየት ብንሞክርም ውይይታችን ምንም ትርጉም ያለው ነገር አላስገኘም። ውይይት ካለማስተዋል ምንም ጥቅም የለውም። ለምሳሌ ቀይ ጃኬቱን ለምን እንደለበሰች ብትጠይቃት ቀለሙ ቀይ ሳይሆን ቡናማ መሆኑን በመናገር ምላሹን ትጀምራለች። ባህሪዋን ከማሻሻል ይልቅ የኔን ምላሽ ትወቅሳለች። ስለዚህም በመካከላችን የነበሩት ውይይቶች ምንም ፋይዳ የሌላቸው ነበሩ። ስለዚህም ብዙ ጊዜ ከመወያየት ይልቅ እሷን ይቅር ማለትን እመርጣለሁ፤ ነገር ግን ይህ በእኔ በኩል ቅሬታን ፈጠረ። ይህም አንዳንድ ጊዜ በጥቃቅን ነገሮች የምናደድ ያስመስልብኝ ነበር።


በተፈጥሮዬ ከብዙ ሰው ጋር መገናኘት ብዙም ስለማልወድ ሁልጊዜም ጓደኞቼ በቁጥር ደረጃ ትንሽ ለማድረግ እጥራለሁ። እናም ስለ እኔ የተናፈሰው ወሬ ራሴን ከዚህ ማህበረሰብ የበለጠ እንዳገል አድርጎኛል።

ሃሜትና አሉባልታ እንዲፈጠሩ ዋናው ምክንያት የጀመረው አካል ብስለት የጎደለው በመሆኑ ይመስለኛል። አሉባልታና ሃሜትን በመጀመራቸውና በማሰራጨታቸው ተጠያቂ እነዚህን የሚያናፍሱ ሰዎች ቢሆንም፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ላለው አለመብሰል ዋነኛው ምክንያት የእርስ በእርስ ግንኙነቶቸን ለመፍጠርና ግጭቶችን ለመፍታት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትርጉም ያለው የውይይት መድረክ አለመኖሩ ነው።

አንዳንድ ጊዜ አለመግባባቶች እና የውይይት እጦት በግንኙነቶች ውስጥ ትልቅ አለመግባባት ይፈጥራሉ። እና ይህ አለመግባባት አንዳንድ ጊዜ ወደ ወሬነት ሊለወጥ ይችላል።

በተጨማሪም የጓደኝነት ግሩፕን አስተውሎ አለመምረጥ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሐሜት እንዲስፋፋ ይረዳል። ጭንቀታችንን እና ስጋትእንን ለነሱ ስናካፍላቸው ሚስጥሮቻችንን አይጠብቁም ይልቅስ ጉዳዮችችንን ወይም ስጋቶችህን ለሌሎች ሰዎች ለማስተላለፍ ይጣደፋሉ።

ማህበረሰባችን ራሱ ትንሽ መሆኑ ተጨማሪ እሳትን ይጨምራል። ሰዎች ራሳቸውን



ለመፈተሽ ዝግጁ አይሆኑም እና ከጓደኞቻቸው ጋር ብቻም ይገናኛሉ እና ይዝናናሉ። በህብረተሰባችን ውስጥ አሉባልታዎችን በፍጥነት ለማሰራጨት የሰዎች ስብስብ በቡድን መደራጀቱ ዋንኛው ምክንያት ይመስለኛል።



እንዲሁም፣ በአብዛኛዎቹ የኲዊር ግንኙነቶች፣ በተለይም በሌዝቢያኖች መካከል፣ ግራ የሚያጋባ መተሳሰር እና አጋራችንን የማጣት ፍራቻ አለ። ብዙ ጊዜ፣ የፈለጉትን እንዲያደርጉ እየፈቀድንላቸውም ያለማቋረጥም ይቅር ስንላቸው እንገኛለን። ይህ አጋሮች እርስ በርስ እንዳይከባበሩ የሚያስችል ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ይፈጥራል። አሉባልታዎች፣ ወሬዎች፣ አለማክበር እና ሌሎች መርዛማ ነገሮች ወደ ግንኙነታችን ውስጥ የሚገቡበት መንገድ ያገኛሉ።

የጓደኛ ቡድናችን የተሻለ መንገድ ስለማያውቁ እና እኛን ለመደገፍ የሚረዱ መሳሪያዎች ስለሌላቸው በእሳት ላይ ነዳጅ መጨመር ብቻ ነው የሚችሉት። እነሱ ራሳቸውን የተሻለ መረዳት ስለሌላቸው ከማህበረሰቡ ጋር ጤናማ እና በአክብሮት የሚኖሩበትን መንገድ ማስተዋወቅ አይችሉም። ስለዚህ በሚያሳዝን ሁኔታ የኲዊር ማህበረሰብ የመርዛማነት አዙሪት ይቀጥላል።

የጓደኛ ቡድናችን የተሻለ መንገድ ስለማያውቁ እና እኛን ለመደገፍ የሚረዱ መሳሪያዎች ስለሌላቸው በእሳት ላይ ነዳጅ መጨመር ብቻ ነው የሚችሉት።





# በባይ እና በፓን መደምሰስ ዙሪያ ያሉ ውይይቶች

ባይሴክሹዋል ወይም ፓንሴክሹዋል ሰዎች ከሚያጋጥሟቸው ትልቁ ፈተናዎች አንዱ እምነት ማጣት ነው። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ እና እንዲሁም በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉት ራሳቸው ባይሴክሹዋል ወይም ፓንሴክሹዋል ሰዎች ከአንድ ሰው ጋር የተገደበ ግንኙነት ውስጥ መሆን እንደምንችል አያስቡም። እኛ ላይ እምነት መጣል እንደሚንቻል አድርገው አያስቡም፣ ጥልቅ ስሜት እንዳለንና እና ልንጎዳ እንደምንችል አያምኑም። አብዛኞቻችን እንደ ስዊንገር፣ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ሰው ጋር ብቻ የፍቅር ግንኙነት የምንመሰርት ወይም የኛ ኩዊርነት ጊዜያዊ ብቻ አድርጎ ነው የሚመለከተው። አንዲት ሴት ባይ ወይም ፓን ከሆነች ለጊዜው ነው እንጂ መጨረሻ ላይ ወደ ተቃራኒ ፆታ አፍቃሪነት ትመለሳለች ብለው ያስባሉ። ወንድ ከሆነ ደግሞ ጌይነቱን መቀበል ስላቃተው ወይም መቀበል ስላስፈራው ብቻ ነው ባን ወይም ባይ ነኝ የሚለው ብለው ይደመድማሉ።

በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የባይ/ፓን ማንነቴን የመሰረዝ እና የመጥላት ሁኔታ በጣም አጋጥሞኛል። እንደ ፓንሴክሹዋል፣ በኩዊር ማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ሰዎች የማይመስልና እና እውነተኛ ማንነት እንዳልሆነ ያስባሉ። ባይ ወይም ፓን መሆን ምን ማለት እንደሆነ በትክክል አይረዱም እና ስሜታችንን ለማወቅ አይሞክሩም።

በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ የባይ/ ፓን ማንነቴን የመሰረዝ እና የመጥላት ሁኔታ በጣም አጋጥሞኛል።

እነሱ ደግሞ ባይ እና ፓን ሰዎችን የሚያዩት ከማንም ጋር ዝም ብሎ ልቅ እና ተራ ግንኙነት የሚያደርጉ እንጂ ቁም ነገር ያለው የረጅም እና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችሉ ሰዎች አይደለም። ስለዚህ በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉት ፓን እና ባይ ሰዎችን የሚመርጡት ለጊዜያዊ ስሜት ማርኪያ ሲሆን በጓደኝነትም ሲቀርቡን ከጥቅም ጋር በተያያዝ መልኩ ነው። አብዛኛዎቹ ኩዊር ሰዎች በምንገናኘው የማህበራዊ ሚድያ እንኳን አንድ ሰው የእኔን ፓንሴክሹዋል በሚያውቅበት ደቂቃ በጣም ወሲባዊ ንቁ ሰው እና ያልተረጋጋ ሰው እንደሆንኩ ነው የሚያስቡት። ሰዎች ከእኔ ጋር ግንኙነት ከጀመሩ እራሳቸውን ከጉዳት ለመከላከል በተጠንቀቅ ተዘጋጅተው ከመሆኑም በላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸውም ከእኔ ጋር የጠበቀ ማንኛውንም ነገር ያስወግዳሉ። ይሄም ፓን ወይም ባይ መሆን ከሁሉም ሰው ጋር መተኛት ብቻ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። ፓን ወይም ባይ መሆን ወላዋይ መሆን ነው ብለውም ያስባሉ።

በኩዊር ስብሰባዎች ወይም ፓርቲዎች ላይም እንኳን የመጋበዝ ዕድል ብዙም የለንም። ሰዎች በቀላሉ እኛን መጋበዝን አያስታውሱም ምክንያቱም እኛን እንደ የኩዊር ማህበረሰብ አካል አድርገው አያስቡንም። ለኩዊር ሴቶች በተዘጋጁ ዝግጅቶች ወቅት፣ በአብዛኛው ሌዝቢያን የሆኑ ሴቶች ብቻ ነው የሚጋበዙት። አልፎ አልፎም ስንጋበዝ፣ በፓርቲው ላይ ያሉ ሰዎች ከሌሎች ሌዝቢያኖች ወይም ጌይ ወንዶች ጋር እንደሚያደርጉት ከእኛ ጋር አብሮ ለማውራት ወይንም ለመጫወት ብዙም ፍላጎት የላቸውም።

ይህ በራስ የመተማመን ስሜት እንዳይሰማኝ እና ብቸኝነት እንዲሰማኝ አድርጎኛል እና ራሴን እንዳገልም የበለጠ ይገፋፋኛል። በርግጥ ምንም ያህል

... አንድ ሰው የእኔን ፓንሴክሹዋልነት በሚያውቅበት ደቂቃ በጣም ወሲባዊ እና ያልተረጋጋ ሰው እንደሆንኩ ነው የሚያስበው።

መጥፎ ነገር ቢመጣም የማህበረሰቡ አባል እንደሆንኩ ይሰማኛል። እኔ የማስበው ከኩዊር ከማህበረሰብ ውስጥ ሆኜ ወደ ውጭ የምመለከት እንጂ ከውጪ ሆኜ ወደ ኩዊር ማህበረሰብ እንድምመለከት አይደለም። በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ባይፎቢያ እና ፓንፎቢያ ያሉ መርዛማ ነገሮች፤ ሲከሰቱም አይቻለሁ እናም አሉታዊ ተፅእኖ አለው ነገር ግን በጣም መጥፎ ስሜት እንዳይሰማኝ ለማድረግ እሞክራለሁ። ህብረተሰቡ ማንነታችንን እና ተሞክሯዋችን ላይ የሚያደርሰውን መርዘኛ ባህሪ ለተለያዩ ማንነቶች እና ልምዶች ካለመጋለጥ የመጣ እንጂ ከክፋት የመነጨ እንዳልሆነ ለመረዳት እሞክራለሁ።

ኩዊር ማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል የጀመርኩት ፓንሴክሹዋልነቴ ካወቅኩኝ  እና ራሴን ከተቀበልኩኝ በኋላ መሆኑ በጣም ረድቷኛል። ማህበረሰብ መኖር ጥሩ ነገር ቢሆንም፣ እኔም ግን ምንም የሚገጥመኝ ነገር ጊዜያዊ ችግር እንደሆን እርግጠኛ ነኝ። ዋናው ነገር እራሴን መቀበል ነበር እናም በዚህ ምክንያት ከልዩነቶቹ ጋር ወደ ማህበረሰቡ መምጣትን ተምሬያለሁ። የተሻለ ስምምነት ከኩዊር ማህበረሰቡ ጋር ሊሰጠኝ እንደሚችል ባምንም ስለ ፓንሴክሹዋልነቴ በጭራሽ አልዋሽም። አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ለማቅለል ስል ብቻ ስለማንነቴ ለማንሳት እንገራግራለሁኝ። ይሄም ሰው የሚሰነዝረው ፍርድን ለማስወገድ ስል ብቻ ነው።

ይህ የማንነቴ ድምሰሳ በአእምሮ ጤንነቴ ላይ ተጽእኖ አለው። አንዳንድ ጊዜ በጣም የመንፈስ ጭንቀት ስለሚሰማኝ ከሰዎች ጋር መነጋገር እንኳን አልፈልግም፤ ሌላም ከፍተኛ ማህበራዊ ጭንቀት ያጋጥመኛል። ሁልጊዜ ሁሉንም ነገር ከመጠን በላይ አሰላስላለሁ እናም በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ስሆን የተሳሳቱ ነገሮችን ላለመናገር አተኩራለሁ። ስለ ሰዎች ግንዛቤ እጨነቃለሁ እና አንዳንድ ጊዜ ከኩዊር ማህበረሰብ መራቅን እመርጣለሁ። ከአእምሮ ጭንቀት ለማዳንም ከኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ከመገናኘት እራሴን አቆጥባለሁ።

ከኩዊር ማህበረሰብ ጋር ያለኝ ግንኙነት አንዳንድ ጊዜ ከሌላው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር ከመገናኘት ጋር ካለኝ ልምዴ የተለየ ሆኖ አይሰማኝም። ህብረተሰባችን ኩዊር መሆን “ነጮች ከውጭ ያመጡት” ነገር ነው ብሎ ያስባል፣ ይህም ማለት እኛ ኩዊር እንድንሆን ያደረገን ለምእራባውያን የኤልጂቢቲኪው+ ፊልሞች፣ ሙዚቃ እና ሌሎች የጥበብ ስራዎች መጋለጥ ነው ብለው ያስባሉ። ኩዊር መሆን በጠቅላላ የኛ ባህል አይደለም ብለው ያምናሉ። ኩዊር ማህበረሰቡ ደግሞ ባይ ወይም ፓን መሆን ቀልድ እንደሆነ ወይም እንደ አላፊ ምዕራፍ እንደሆን አድርገው ያስቡታል። ስለዚህ ማንነታችን እያንዳንዱ ሰው የማይቀበለው እና የሚሳለቅበት አይነት ይሆናል።

የኩዊር ማህበረሰብ ከምንም ነገር በፊት እንዲረዳን እና ፓን እና ባይ የሆኑ ሰዎችን ማንነት እንዲያውቅ በእውነት እፈልጋለሁ። ስለ እኛ ማንነት ያላቸውን የተዛባ ግንዛቤ አጥፍተው ከራሳቸው የሕይወት መርሆች አንፃር ነገሮችን እንዲረዱ እና እንዲሰሩ እፈልጋለሁ።

ሁሉም ሰው እርስ በርስ ለመረዳዳት ከሰራ እና ሁላችንም ያለመተማመንን ወይም የመተውን ፍራቻ ከተውን በመካከላችን ያለው መርዛማ ግንኙነት ይጠፋል። ተቀባይነት እንዲኖረን ወይም ሌሎች ለእኛ ቦታ እንዲፈጥሩ ማስገደድ አያስፈልገንም ምክንያቱም እንደ እኔ እምነት እነዚህን ነገሮች በደንብ ከፈተሽን ያለምንም ጭንቀት እነዚህን ጥልቅ ጉዳዮች መፍታት የምንችልበት መንገድ ይመጣል።

# ጥላውን ማሰስ፡ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለው መርዛማነት



ማህበራዊ ሚድያ እንደ ግድግዳ
ጀርባ መደበቅ ስለሆነ ሰው ማንነቱን
አታውቂውም እናም ይህንን ተገን
በማድረግ ብዙ ብልግና ይራመዳል።



# የድሮ ፍቅረኛዬ እኔ የማላውቀው የፌክ አካውንት ከፍታ በፌክ አካውንቴ ላይ በፌስቡክ ፅፋልኝ ነበር።

ከስም አልባ ግድግዳ ጀርባ መሆን ብዙ መዘዝ ያመጣል። እኔ ኩዊር ሰዎች ማህበራዊ ሚዲያን እርስ በርስ ለመገናኘት በሰፊው መጠቀም ሲጀምሩ የረጅም ጊዜ የፍቅር ግንኙት ውስጥ ስለነበርኩኝ ብዙም የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ አልነበርኩም። ግን ያው ጓደኞቼ ሲጠቀሙ እመለከት ስለነበር የዚህን ያህል አዲስ ነገርም አልሆነብኝም።

ማህበራዊ ሚዲያን ስለዚህም ይምስለኛል የፍቅር ግንኙነቴ ተቋርጧ እኔም ተሳታፊ መሆን ስጀምር ያው ጠንቃቃና ብልህ ሆኜ የገባሁበት። ይህንን ስል እኔም ግድግዳውን ተገን አድርጌ ጥፋቶች አላጠፋሁም እያልኩ አይደለም። የሰው ፕሮፋይልን በተደጋጋሚ ከፍቼ በማየት ስለነሱ ምን መማር እንደምችል አይ ነበር። በተጨማሪም አንድ ሁለት ሰዎች ጋር ረዘም ያለ ወሬ አውርቼ ያለምንም ማስረዳት የጠፋሁበት ሁኔታ አለ። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ያደረኳቸው ነገሮች ጊዜዬን ያባኩ፤ አላስፈላጊ እና ለሌላም ሰው ጎጂ ነበሩ ብዬ አምናለሁ።

ማህበራዊ ሚዲያ ላይ መርዛማ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። በተለይ ፌስቡክ ላይ ብዙ የኩዊር ሰዎች ተመሳሳይ ፆታ ጠል ማህበረሰብ ውስጥ ስለምንኖር በአካውንታችን ማንነታችንን ለመደበቅ ስንል በሌላ ስም ነው የምንከፍተው። ማንነትን መደበቅ ሃሳባችንን እንድንናገር እና እራሳችንን ሳናጋልጥ ከሌሎች መሰል ሰዎች ጋር እንድንገናኝ መንገድ ይፈጥርልናል። ነገር ግን ማንም ሰው ትክክለኛ ስሙን ስለማይገልፅ ከግድግዳው ጀርባ ከማን ጋር እያወራሽ እንደሆነ አታውቂም። በአንድ በኩል ይሄ የራሱ የሆነ የሚያስጨንቅ ነገር አለው ምክንያቱም የመፍራት እና ሁሉን ነገር ግልፅ ያለ ማድረግ ነገር አለ።

አንዳንድ ጊዜም እያናገርሻቸው ያሉት ሰዎች የማህበረሰቡ አባል ያልሆኑ ወይንም “ሙከራ” እያደረጉ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንደውም በግሌ የሰማሁት አንዴ አንድ ቀጥ ወንዶች ሴት እና ሌዝቢያን ነኝ ብለው ቀጥረው ለማግኘት የሞከሩ አለ። ጓደኛዬንም ተመሳሳይ ነገር አጋጥሟታል። ስለዚህ ያስፈራል፤ በነጻነት የምትፈልጊውን ሀሳብ መጋራት እና ማውራት አትችይም። ፌስቡክ ላይ ከተገናኘሽ በኋላ ፎቶ መላክ፣ ስልክ ማውራት እና ስልክ ቁጥር መስጠት ድረስ ያለው ነገር አስፈሪና ሰላም የማይሰጥ ጉዳይ ይሆናል።

ሌላ ማህበረሰቡ አናሳ እንደመሆኑ መጠን አብዛኞቻችን እርስ በእርሳችን እንተዋወቃለን። የምታናገሪው ሰው የማህበረሰቡ አባል እንደሆነ ካወቅሽም በኋላ እና በስልክም ከተነጋገርሽም በኋላ ቢሆን ሙሉ መረጃሽን ማጋራት በጣም ይከብዳል። ሊጎዳሽ የሚችል ነገር ሊያደርጉ እንደሚችሉ ትገምቻለሽ። በዛ ላይ የማታውቂውን ሰው በአነጋገሩ ሰውን መገመት ስለማይቻል ጥሩ ሰው አገኘሁ ብለሽ ሙሉ የግል መረጃሽን ስታካፍይ የሚመጣብሽ ሌላ ነገር ሊኖር ስለሚችል ፍራቻና ያለመረጋጋት ስሜትም ያመጣል።

አንቺ እና እኔ ዴት ያደረግነው አንድ አይነት ሰው ካለ ሁላችንም እርስበርሳችን ተመቻችተን አናወራም ምክንያቱም “ፍቅረኛሽ እኮ እንደዚህ ብላ ጀነጀነኝ” የሚባል ሃሜት ወይም ወሬ እንዳይመጣ ስለምንሰጋ ነው። ብታወሪም ላይ ላዩን እንጂ የውስጥሽን ለማውራት አይመችም፤ ስለምትፈሪ ትንሽ ትጠነቀቂያለሽ። ጭራሽኑ ደግሞ የራስሽ የድሮ ፍቅረኛ በሌላ ፌክ አካውንት ትሞክርሻለች እና ሳታውቂ አንዳንድ ነገር ልታወሪ ትችያለሽ እና ይሄም ደስ የማይል ስሜት እንዲሰማሽ ያደርጋል።

ማህበራዊ ሚድያ እንደ ግድግዳ ጀርባ መደበቅ ስለሆነ ሰው ማንነቱን አታውቂውም እናም ይህንን ተገን በማድረግ ብዙ ብልግና ይራመዳል። ያለምንም ፍቃድ መጠየቅ ራቁት የሆኑ ፎቶዎች እና ቪዲዮዎች መላላክ፣ ከፖርን የማይተናነሱ ነገሮችን በምስል፣ በድምፅ እና በቴክስትም መላክ የተለመደ ነው።

ይሄ ሁሉ ነገር ስላለ ከማን ጋር አምነሽ ምን እንደምታወሪ ግራ ነው የሚገባሽ። ወሬ እንኳን ምን ብለሽ መጀመርን እንዳለብሽ ይጠፋሻል። ድሮ ሰውን በአካል ስለሆነ የምንተዋወቀው ዘሎ አንዳንድ ነገር ውስጥ አይገባም፤ ሰው እርስ በርሱ እስኪግባባ ድረስ ጊዜ ይወስዳል። እላፊ ነገርም መናገር ሊያስገምተው እንደሚችል ስለሚያውቅ ከብልግና ንግግር ይታቃባል። ብልግናው ጋር ባይደርስም ሌሎችም ብዙ መርዛማ የሆኑ ነገሮች ሰውን ይፈትናሉ።

እኔም ላይ አንዳንድ ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች ደርሰውብኝ ያውቃሉ። ለምሳሌ የድሮ ፍቅረኛዬ እኔ የማላውቀው የፌክ አካውንት ከፍታ በፌክ አካውንቴ ላይ በፌስቡክ ፅፋልኝ ነበር። አዋርታኝ የሌላ ሰው ፎቶግራፍም ልካልኛለች። የሷ አካውንት እንደሆነ ሰላማላውቅ ልታስለፈልፈኝ እና ልትሰልለኝ መሆኑ ነው። ሌላ እሷን የሚያውቁ ሰዎች በፌክ ኤካውንታቸው አዋርተውኝ ለሷ ሄደው እንደዚህ አለች ብለዋት ያውቃሉ። እሷም ደግሞ በፌዝም በቀልድም እንደሰማች ነግራኛለች። ሀሜት እና ወሬ በጣም ይናፈሳል፤ እገሌ እንደዚ ብላለች በዚህ መልስ ሰጠች የሚባሉ ብዙ የወሬ ማቀባበሎች ያጋጥመኛል። ጉዳይሽ በሙሉ በቀላሉ ሁሉ ቦታ ይደርሳል።

ሌላው ያጋጠመኝ ነገር ፌስቡክ ላይ በፌክ አካውንት ካወሩሽና ብዙ መንገድ ከሄዱ በኋላ ለፍቅር ግንኙነት ጠይቀውሽ አልፈልግም ስትይ በሰጠሻቸው ፎቶ ተመርኩዘው እውነተኛ አካውንትንሽ አግኝተው ክፉ ነገር ለማድረስ ለማስፈራራት ሲሞክሩ አይቻለሁኝ። የበለጠ የሚያሳዝነውም ይህንን የሚያደርጉት እኛው ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች መሆናቸው ነው። አንድ ሰው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ አባል ሆኖ ሌላ ሰውን እንዴት እንደዚህ ማድረግ እንደሚችል አላውቅም ። እንዲያውም አንድ የማውቀው ሰው ይህንን ተግባር ስትፈፅም ደርሼባት በከፍተኛ ሁኔታ ተጣልተናል። ፎቶ ወይንም ድምፅ ይዛ እንደማስፈራሪያ በተከታታይ ትጠቀምበታላች። አንዳንዴም በፌክ አካውንትሽ እንኳን ሰው አምነሽ ባትላላኪም ትክክለኛ እካውንትሽን ስለሚያውቁት እዛ ውስጥ ገብተው ፎቶ ወስደው ማንነትሽን ለማውጣት ይሞክራሉ። አንደዚህም አድርገው ህይወቷን ያመሰቃቀሉባት ልጅ አውቃለሁ።


ይህም እኔ ላይ እናዳይደርስ አሁን የፈለገ ነገር ቢሆን በአካል ለማላውቀው ሰው አምኜ የግል መረጃዬን በፍፁም አልሰጥም። በአካል የማውቀው ሰው ካልሆነ ከቴሌግራም ዩዘርኔም በስተቀር ሌላ ምንም የግል መረጃ አልሰጥም። እንደውም ቴሌግራም ዩዘርኔም ከመስጠቴ በፊት ድምፅ፣ ፎቶግራፍ እና ቪዲዮዎች አጥፍቼ ካልሆነ በምንም ሁኔታ በአካል ለማላውቀው ሰው አልሰጥም።

እኔ በግሌ አላስፈላጊ ነገሮች ስለሚበዙ ከፌስቡክ እና ከሌላ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንድርቅ ተገደጃለሁ። በፊት ፌስቡክ ከሰው ጋር ለመተዋወቅም ሆነ ከኲዊር ሰዎች ጋር ማህበረሰብ ለመፍጠር ወሳኝ መንገድ ነበር። አንድ የድሮ ፍቅረኛዬንም የተዋወኳት ፌስቡክ ላይ ነው። ከመተዋወቅም አልፈን ረጅም ዓመትም አብረን ቆየተን ነበር።

አሁን ላይ ያለው ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል ስለዚህም ፌስቡክን ባመንኩት ልክና ሰው ባገኘሁበት ልክ አሁን አላምነውምም እፈራዋለሁም።


# የኢትዮጵያ LGBTQ+ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ መርዛማ ባህሪያት ጋር ያጋጠሙዎት አለ እና የመከባበር ባህልንስ እንዴት መፍጠር እንችላለን?


## እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...













ባይ ፎቢያ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ምክንያቱም እኛ በተቃራኒ ጾታም ስለምንሳብ እንዴት ትንሽ አድርገው እንደሚያዩን




Nicki Maraj

ሱስ

የበለጠ እንዳስረዳ ከፈለጋችሁ በውስጥ መስመር መላክ እችላለሁ




ሬድ ኤማ

በአገራችን ያሉ አብዛኛዎቹ ሰዎች ሰርተው ገንዘብ ማግኘት አይፈልጉም። ይልቁንስ ሌት ተቀን ፓርቲ ያደርጋሉ። ትልቅ ችሎታ ያገኙ ይመስል ከሁሉም ሰው ጋር ስለመተኛት በኩራት ያወራሉ። ሥራ ለማግኘት ስለሚታገሉ ሰዎች እየተናገርኩ አይደለም። በኔ እምነት እራስን መደገፍ ሲቻል ብቻ ነው በነፃነት መኖር የሚቻለው። በተለይ እንደኛ ባለ ሀገር የተረጋጋ ገቢ ሊኖር ይገባል። ነገሮች እንዲለወጡ ከፈለግን ለውጥ ማምጣት የምንችልበት ደረጃ ላይ መድረስ አለብን። ፖለቲከኞች፣ ሀብታም ነጋዴዎች፣ ስኬታማ የግንባታ ሰራተኞች፣ ዶክተሮች፣ ዘጋቢዎች፣ ... ህይወታችን/ወሲባዊ ማንነታችን ጊዜያዊ አይደለም። ለኛም ሆነ ለሌሎች መልካም መፃኢ ዕድል ከፈለግን ይህንን ማወቅ ፤ አለብን ማንም የማይነቀን ሰዎች መሆን አለብን።